# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 301 ሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# “ኢትዮጵያን ለማጽናት ሰው ሲሞት የምንጮህና ከዚያ የምንረሳ መሆን የለብንም”

- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን ለማጽናት ሰው ሲሞት ብቻ እየጮህን ከዚያ የምንረሳ መሆን የለብንም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

በትናንትናው ዕለት በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 16ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ የሰጡት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያን በዘላቂነት ለማጽናት ጠላቶቻንን በሙሉ ኃይል መከላከል ይጠበቅብናል።

እስካሁን በመጣንበት ሂደትም ጠላቶቻችንን ለመከላከል እና ዜጎቻችንን ለመጠበቅ ብዙ መንገድ ተጉዘናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ያም ሆኖ ግን አሁንም ብዙ ጥረት ያስፈልገናል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን ለማዳከም የሚከተሉት ስልት ብዙ መልክ ያለው ነው። በመዋቅር ውስጥ ሰው መግዛት፤ የተቀናጀ የሚዲያ ዘመቻ እና ባንዳዎችን በመጠቀም ሀገርን ማተራመስ ዋነኛ ስልታቸው እንደሆነ ጠቁመዋል።

ተላላኪዎቻቸውም ይህንን ለማስፈጸም በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተሉ መሆኑን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የራሳቸው እግር የሌላቸው ሸኔና ሌሎች የሸብር ቡድኖች እግር የሚገጥምላቸው አካል ሲያገኙ በየቦታው ጥፋት ይፈጽማሉ ብለዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በንጹሓን ዜጎች ላይ የሚደርሰውን ግድያ ለማስቀረት የጸጥታ አካላትና



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

“ኢትዮጵያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ኦሮሚያን ይጎብኙ
የብዝሃ-ውበት ምድር!



Website:
https://www.visitoromia.org
Facebook:
https://www.facebook.com/visitoromia/
Instagram:
https://instagram.com/VisitOromia
Twitter:
https://twitter.com/VisitOromia
LinkedIn:
https://linkedin.com/company/visitoromia
YouTube:
https://YouTube.com/visitoromia
Pinterest:
https://Pinterest.com/visit_oromia
Telegram:
https://t.me/visit_oromia
ኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን
www.visitoromia.org


# “ኢትዮጵያ ወደ ዳገት ስምታደርገው ጉዞ የምክር ቤት አባላትና ሀገር ወዳድ ዜጎች ድጋፍ ማድረግ ይገባቸዋል”

- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

ፍቃዱ ዴሪሳ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ወደ ዳገት ለምታደርገው ጉዞ የምክር ቤት አባላትና ሀገር ወዳድ ዜጎች ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባቸው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በትላንትናው እለት ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ወቅታዊና ሀገራዊ ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ወደ ዳገት የምታደርገው ጉዞ በጣም ቅርብ የሆነ፤ ነገር ግን

“ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የፌዴራል መንግሥት በጀት 786 ነጥብ 61 ቢሊዮን ብር ሆኖ ፀደቀ

## - ከበጀቱ 59 በመቶ ለድህነት ቅነሳ ይውላል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የ2015 ዓ.ም የፌዴራል መንግሥት በጀት 786 ነጥብ 61 ቢሊዮን ብር አድርጎ በአራት ድምፀ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምፅ አፅድቋል፡፡

6ኛው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 16ኛ መደበኛ ስብሰባ በትናንትናው ዕለት በ2015 ዓ.ም የፌዴራል በጀትን መርምሮ ማፅደቅ እና በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሚደረግ ውይይት ላይ ትኩረቱን ያደረገ ስብሰባ አካሂዷል፡፡ ረቂቅ በጀቱን ዝርዝር የተመለከተው የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ማብራሪያዎችን ከሰጠ በኋላም የ2015 ዓ.ም የፌዴራል መንግሥት በጀት 786 ነጥብ 61 ቢሊዮን ብር ሆኖ በአራት ድምፀ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምፅ እንዲፀድቅ ወስኗል፡፡

በዕለቱ ተገኝተው የ2015 ዓ.ም በጀት የትኩረት

የፌዴራል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ከ25 ሺህ በላይ ቤቶች ለባለ ዕድለኞች ይተላለፋሉ

ገጽ 4


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር




0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today'
+251 111 26 34 34
united.insurance@unic-ethiopia.com
ለ ሁሉም የመድን ፍላጎትዎ
ለህይወት
ህጋዊ ግዴታዎ

# የአዲስ አበባ የትምህርት ማኅበረሰብ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ተጀመረ

**ሙሳ ሙሐመድ**



አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ የትምህርት ማኅበረሰብ የ2014 ዓ.ም የክረምት የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ተጀመረ። በተያዘው ክረምት ወቅት በትምህርት ማኅበረሰቡና አመራሮች ብቻ ከሶስት ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ወደ ተግባር መግባቱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ ትናንት በተካሄደው የችግኝ ተከላ ማስጀመሪያ መርሐ- ግብር ላይ እንደገለጹት፣ በዘንድሮው የክረምት የአረንጓዴ አሻራ የማኖር መርሐ-ግብር ከ200ሺህ በላይ የትምህርት ማኅበረሰብና አመራሮች በማሳተፍ ከሶስት ሚሊዮን በላይ ችግኞች ይተከላሉ። ችግኞችን የመትከል ማስጀመሪያ መርሐ- ግብሩም ከሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በየካ ሚሊኒየም ፓርክ ይፋ ሆኗል።

በዚህ “አሻራችን ለትውልዳችን” በሚል መሪ ቃል በየካ ሚሊኒየም ፓርክ በተጀመረው አራተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ የማኖር የችግኝ ተከላ መርሐ-ግብር ከሶስት ሚሊዮን በላይ ችግኞች የሚተከሉ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህ መርሐ ግብርም የትምህርት ማኅበረሰብ ብቻ በማሳተፍ የሚከናወን መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ዘላለም ገለጻ፤ በመርሐ-ግብሩ በኅብረት ችግኞችን እየተከልን የደን ሽፋናችንን የምናሳድግበት ነው። አረንጓዴ ልማትን ማፋጠናችን ተፈጥሮን ከመንከባከብ ባሻገር በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሌም አብረን እንደምንቆም ማሳያችን ነው።

የተፈጥሮን ሚዛን እየጠበቁ ማደግን ካደጉ ሀገራት ልንማር ይገባናል ያሉት አቶ ዘላለም፤ በአየር ንብረት ለውጥ የሚታመሱና በተፈጥሮ አደጋ ዜጎቻቸውን የሚያጡ ሀገራትም ቁጥር ቀላል አይደለም። ከዚህ በመማር ከወዲሁ የአረጓዴ አሻራ የማኖር መርሐ-ግብርን መሳተፍና መደገፍ ወሳኝ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለተከታታይ አራት ዓመታት እያካሄደችው ያለውን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለአየር ንብረት ለውጥ መከሰትና መባባስ ትልቅ ሚና ያላቸው ሀገራት ሳይቀሩ እውቅናና ድጋፍ እየሰጡት ይገኛሉ ያሉት አቶ ዘላለም፤ ይህ ለኢትዮጵያ ትልቅ ስኬት መሆኑን ገልጸዋል።

ሀገራችን የነደፈችው የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ መርሐ-ግብር የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑን አመልክተው፤ በአፈር መሸርሸር የተጎዱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ፣ የወደሙ ደኖች እንዲመለሱ የችግኝ ተከላ ፋይዳው የጎላ ነው ብለዋል አቶ ዘላለም።

በመርሐ-ግብሩ ዜጎች ከጫፍ ጫፍ በመነሳት ለአገራቸው ችግኝ ለመትከል እያደረጉት ያለው እንቅስቃሴን ታሪክ እንደማይረሳው ገልጸው፤ ኢትዮጵያ እያከናወነችው ያለችው ዘላቂ የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር የሀገራችንና የዓለማችንን የተፈጥሮ ሀብትን ጠብቆ ለማቆየት ሁነኛ መፍትሔ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሪት ፋኢዛ ሙሐመድ በበኩላቸው በዘንድሮው የችግኝ ተከላ መርሐ-ግብርም ከ200 ሺህ በላይ የሚሆኑ በአዲስ አበባና በዙሪያዋ የሚገኙ የትምህርት ማኅበረሰብ ወገኖች ይሳተፉበታል ብለዋል።

እንደ ወይዘሪት ፋኢዛ ገለጻ፣ እየተከልን ያለነው ችግኝ በአየር ንብረት ለውጥን ምክንያት የሚደርሰውን የአካባቢ መራቆትና የተፈጥሮ አደጋ ከመከላከል ባሻገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል ። በዘንድሮው የችግኝ ተከላ መርሐ-ግብርም ችግኞችን ከመትከል ባለፈ እንዲፀድቁ መንከባከብ ያስፈልጋል ።

## ‹‹ምክንያታዊ ያልሆነ ትውልድ እየተፈጠረ ያለው ሀገራዊ የንባብ ባሕል በመዳከሙ ነው››

- አቶ አበረ አዳሙ

የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ፕሬዚዳንት

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- አገራዊ የንባብ ባሕል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ በመምጣቱ ግደል ሲባል ለምን ብሎ የማይጠይቅ ምክንያታዊ ያልሆነ ትውልድ እየተፈጠረ መሆኑን የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ አበረ አዳሙ ገለጹ፡፡

አቶ አበረ አዳሙ ዓመታዊው ‹‹ሰኔ 30 የንባብ ቀን›› መርሐ ግብር ትናንት በአብርሆት ቤተ መጽሐፍት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር ያለው የንባብ ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከመ መጥቷል፡፡ በዚህም ምክንያት እከሌን ግደል ሲባል ለምን ብሎ ምክንያት የማይጠይቅ ትውልድ እየተፈጠረ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር አገራዊ የንባብ ባሕልን ለማሳደግ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ 30ን የንባብ ቀን ብሎ እንዲያውጅ ተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ሆኖም ከምክር ቤቱ ጉዳዩ የሦስተኛ ወገን ጥቅም የማይነካና ጠቃሚ ሀሳብ በመሆኑ ማኅበሩ ሰኔ 30ን የንባብ ቀን ብሎ ማወጅ ይችላል የሚል ምላሽ በማግኘቱ ቀኑን መሰየሙን ተናግረዋል፡፡

አንባቢ ትውልድ በተፈጠረ ቁጥር በርካታ ደራስያንን ማፍራት ያስችላል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ መጻሕፍት የአዕምሮ ስብራትን በመጠገን ሀገርን የሚገነባ ትውልድ ለመፍጠር ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ ፖለቲከኞች፣ የሃይማኖት አባቶችና ታዋቂ ግለሰቦች ንባብ ላይ ያለውን መቀዛቀዝ ለማሻሻል የሚደረገውን ጥረት እንዲያግዙን እንፈልጋለን ብለዋል፡፡

ቀደም ሲል ትምህርትና ሃይማኖት ተቋማት ላይ በተሠራው ያልተገባ ሥራ ኢትዮጵያዊ ሥነምግባር እንዲጠፋ፣ መከባበርና መተባበር እንዲከስም እና ምሑራን ከአገር እንዲሸሹ መደረጉን አስታውሰው፤ አንባቢ ትውልድ በመፍጠር ትውልዱን ወደ መሠረቱ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መገናኛ ብዙኃንን ጨምሮ ሌሎችም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

ትምህርት ቤቶች ከተዘጉ በኋላ ወጣቶች ጊዜያቸውን የት ያሳልፋሉ የሚለው ማኅበሩን ያሳስበዋል ያሉት አቶ አበረ፤ ሰኔ 30 የንባብ ቀን እንዲሆን የተፈለገው በክረምት ወቅት የንባብ ንቅናቄ በመፍጠር ወጣቶች አልባሌ ቦታዎች ከመዋል ይልቅ ጊዜያቸውን በንባብ እንዲያሳልፉ ለማበረታታት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ትምህርት ቤቶች፣ ፍርድ ቤቶችና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ጭምር ሰኔ ላይ እንደሚዘጋ አስታውሰው፤ ይህን ጊዜ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም አዕምሮው በንባብ የበለጸገና በምክንያት የሚደግፍና የሚቃወም ትውልድ ለማፍራት የተጠናከረ ዘመቻ እንደሚደረግም ጠቁመዋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ አንጋፋና ወጣት ደራሲያንን ጨምሮ ሌሎችም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተገኙ ሲሆን፣ ደራስያንና ንባብ ላይ እየሠሩ ያሉ ግለሰቦች የንባብ ልምዳቸውን ለታዳሚዎች አካፍለዋል፡፡

# ሽልማቱ

## የጥበብ ባለሙያዎችን ለበለጠ ውጤት እንደሚያነሳሳ ተገለጸ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ጉልበታቸውን፣ ጊዜያቸውንና ሃብታቸውን መስዋዕት በማድረግ የጥበብ ማዕድ ለሕዝብ እያቀረቡ የሚገኙ የጥበብ ባለሙያዎችን መሸለምና እውቅና መስጠት ባለሙያዎቹን ለበለጠ ውጤት የሚያተጋ መሆኑን የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ ገለጹ።

በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር አዘጋጅነት “ክብር ለጥበብ” በሚል ሁለተኛው የዕውቅና እና ሽልማት መርሐ ግብር በተካሄደበት ወቅት ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ እንደገለጹት፤ በበርካታ ፈተና መካከል በመጓዝ እየወደቁ እና እየተነሱ የጥበብ ማዕድ ለሕዝባቸው ያቀረቡ ባለሙያዎችን መሸለም ለበለጠ ውጤት ያተጋል።

የዕውቅና እና ሽልማት መርሐ ግብሩ የጥበብ ባለሙያዎች ይበልጥ እንዲተጉ፣ በራሳቸው እንዲተማመኑና ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ለማስቻል ጉልህ ሚና እንደሚኖረው፣ የእውቅናና ሽልማት ባለቤቶቹ በቀሪ ዘመናቸው ይበልጥ እንዲተጉ እንደሚያደርጋቸውም ነው የጠቆሙት።

ሽልማት ወይም እውቅና የሚበረከተው በጥበብ የተሞላ ውጤታማና አመርቂ ሥራዎችን በመሥራት በኅብረተሰቡ ዘንድ ለሚታወቁ ወይንም ልዩ ተሰጥኦ ላላቸውና በሥራቸው ለሌሎች ተምሳሌት መሆን ለቻሉ ባለሙያዎች መሆኑንም አመልክተዋል።

የሽልማት ሥነ ሥርዓት በየጊዜው መኖር አስፈላጊ መሆኑን በመጠቆምም፤ ተሸላሚዎች ሥራዎቻቸው ዋጋ እንዳለው በመገንዘብ ለበለጠ ውጤት ተግተው እንዲሠሩ ለማበረታታት፣ በራስ መተማመንና ተነሳሽነትን እንዲፈጥሩ እንደሚያደርግም አመልክተዋል።

ጥበበኞችን ማክበርና መንከባከብ ያስፈልጋል። ሁላችንም ጥበበኞች ልንሆን ይገባልም ብለዋል። ከመዋዕለ ሕጻናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ድረስ ጥበብ እንዲከበርና ለሀገር አድገት ማበርከት የሚገባውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክትና ሙያው በሳይንስ ተደግፎ እንዲያድግ ይደረጋልም ነው አቶ ቀጀላ ያሉት።

ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በዕደ ጥበብ፣ በሕንጻ ግንባታ፣ በሙዚቃ፣ በቴያትር፣ በሥነ ጽሑፍ እና በሥነ ስዕልና በመሳሰሉት የጥበብ አይነቶች የተካኑ ባለሙያዎች የሚገኙባት ሀገር ናት። በርካታ ዜጎቿ የጥበብ ሥራዎቻቸውን ለትውልድ አስቀምጠው ማለፋቸውንም አስታውሰዋል።

የሙዚቃው በሙዚቃው ዘርፍ የአውሮፓውያን የጥበብ ሰዎች ብቅ ከማለታቸው በፊት በኢትዮጵያ እነ ቅዱስ ያሬድን የመሳሰሉ የጥበብ ሰዎች እንደነበሩ ታሪክ እንደሚመሰክር አንስተዋል። ደራሲና ጋዜጠኛ በዓሉ ግርማ፣ ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን ከቅርቦቹ የጥበብ ሰዎች አብነት ማንሳት እንደሚቻልም ተናግረዋል።

የቀደምት አያት ቅድመ አያቶች ዜማና ቅላጼ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተላልፈው ባህሎቹ ዘመን አይሽሬ ሆነው ጣዕም ያላቸው ሆነው ቀጥለዋል። እየዳበሩ ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። መጠበቅ እና ማስፋፋት ይገባል ነው ያሉት።

የጥበብ ሥራዎች ማመስገን እና መልካም ሥራዎችን በአደባባይ መመስከር በተለይ በጥበብ ሥራዎች ብዙም የተለመደ ስላልነበር የተለያዩ የጥበብ ሥራዎችን የሠሩ በርካታ የሥነ ጥበብ፣ የኪነጥበብ፣ የዕደ ጥበብና የተለያዩ የጥበብ ባለሙያዎች ሳይሸለሙና ሳይመሰገኑ ማለፋቸውንም ነው ያነሱት።

አቶ ቀጄላ እንዳሉት እውቅና የመስጠት ተግባር በተለያዩ ዘርፎች እየተጀመረ ይገኛል፣ በየመሥሪያ ቤቱም ታታሪ ሠራተኞችን መሸለም እየተለመደ መጥቷል፤ ይህ መበረታታት ይኖርበታል።

# የነዳጅ ድጎማውን በአግባቡ ለመተግበር ሁለት ሺህ ተቆጣጣሪዎች መሠማራታቸው ተጠቆመ

ጌትነት ተስፋማርያም




አዲስ አበባ፡- የታለመለት የነዳጅ ድጎማ አሠራርን በተመለከተ ቁጥጥር የሚያደርጉ ሁለት ሺህ ተቆጣጣሪዎች መሠማራታቸውን የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን አስታወቀ።

የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን የነዳጅ አቅርቦት፣ ስርጭት፣ ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ ዴሬሳ ኮቱ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ባለስልጣኑ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ የታለመለት የነዳጅ ድጎማ አሠራርን የሚቆጣጠሩ ሰዎችን አሰልጥኗል።

ሰልጣኞቹም የነዳጅ ድጎማ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ከሆነበት ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ቁጥጥር የማድረግ ሥራቸውን ጀምረዋል ብለዋል።

ከሁለት ሺህ ተቆጣጣሪዎች ውስጥ 70ዎቹ በአዲስ አበባ ከተማ መሰማራቸውን የገለጹት አቶ ዴሬሳ፤ በመላ አገሪቷ በአጠቃላይ በዘጠኝ ክላስተር የተከፋፈሉ ተቆጣጣሪዎች በተለያዩ ከተማዋና ወረዳዎች ጭምር ተመድበው እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በየአካባቢው የተመደቡ የነዳጅ ድጎማ አፈጻጸም ተቆጣጣሪዎች በየዕለቱ በነዳጅ ማደያዎች ያለውን ክምችት እንዲሁም የነዳጅ ሽያጭ በተመለከተ ቁጥጥር ያደርጋሉ።

በዋናነትም እያንዳንዱ ማደያ የደረሰውን ነዳጅ ጫኝ ቦቴ ተገቢውን ጭነት ይዞ መድረሱንና በአግባቡ ማራገፉን በተመለከተ ማረጋገጫ እንደሚሰጡ አስታውቀዋል።

በየአካባቢው የተሠማሩ ተቆጣጣሪዎች ከፌዴራል፣ ከክልልና ከተማ መስተዳድር ቢሮዎች እንዲሁም ከተለያዩ የትራንስፖርትና የነዳጅ ጉዳይ የሚመለከታቸው ተቋማት የተውጣጡ መሆናቸውን አቶ ዴሬሳ ጠቁመዋል።

ባለሙያዎቹም ከትራንስፖርትና ስምሪት ተቆጣጣሪዎች ጋር በመሆን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቱን ላይ የተደረገው የነዳጅ ድጎማው ለታለመለት አገልግሎት ውሏል ወይ የሚለውን እየተዘዋወሩ እንደሚቆጣጠሩ አቶ ዴሬሳ ገልጸዋል።

ከዚህ ባለፈ የነዳጅ ድጎማው ዓላማ ታችኛውን ኢኮኖሚ ላይ የሚገኘውን ኅብረተሰብ ለመደገፍ በመሆኑ ድጎማውን የወሰዱ አሽከርካሪዎች በተተመነላቸው የትራንስፖርት ዋጋ ኅብረተሰቡን እያገለገሉ ስለመሆኑ ባለሙያዎቹ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚችሉ ተናግረዋል።

ችግር ሲገኝና የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ላልተፈለገ ሕገወጥ አገልግሎት ሲውልም ተቆጣጣሪዎች በየዕለቱ አስፈላጊውን ሪፖርት ያደርጋሉ። በሪፖርቱ መሠረት ችግር የተገኘባቸው ተሽከርካሪዎች ከነዳጅ ድጎማው ኮታ ይነሳሉ፤ አለፍ ሲልም ከትራንስፖርት አገልግሎት ስምሪት እንዲወጡ የሚያደርግ ቅጣት ሊጣልባቸው ይችላል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም ከጂቡቲ ተነስተው ማደያዎቻቸው ጋር መድረስ ከነበረባቸው 200 የነዳጅ ቦቴዎች መካከል 10ሩ ሆን ተብሎ የነዳጅ እጥረት እንዲፈጠር በማድረጋቸው መወረሳቸውን የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ገልጿል። ቀሪዎቹ ቦቴዎች ላይ የተወሰደውን ርምጃ በተመለከተ ግን ለማጣራት ቢሞከርም ንግድ ቢሮውም ሆነ ባለስልጣኑ ዘንድ መልስ አልተገኘም።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ይፋ ባደረገው መረጃ መሠረት፤ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የተለያየ መጠን ያላቸውን ተሽከርካሪዎችን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርገው የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ከሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ከ160 ሺህ በላይ ተሽከርካሪዎች ላይ ተግባራዊ ሆኗል።

በዚህም መሠረት ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ (ባጃጅ) በቀን ሰባት ሊትር፣ መለስተኛ የከተማ ታክሲ (ላዳ) በቀን 25 ሊትር፣ ሚኒባስ ታክሲ በቀን 65 ሊትር፣ መለስተኛ አውቶቡስ በቀን 94 ሊትር፣ የከተማ አውቶብስ በቀን 102 ሊትር፣ ሀገር አቋራጭ አውቶቡስ በቀን 65 ሊትር ነዳጅ መቅዳት እንደሚችሉ ታውቋል።




# የዓለም ባንክ

## ለኢትዮጵያ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገለጸ

አዲስ አበባ፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ከዓለም ባንክ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አክሴል ቫን ትሮትሰንበርግ ጋር በሴኔጋል ዳካር በትናንትናው ዕለት ተወያይተዋል፡፡

አቶ ደመቀ የዓለም ባንክ አካል የሆነው እና አፍሪካ በምታገግምበት ሁኔታ ላይ ድጋፍ የሚሰጠው የዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር (በአይ.ዲ.ኤ 20) የመሪዎች ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ ሴኔጋል ዳካር ገብተዋል።

በዳካር ቆይታቸውም ከዓለም ባንክ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አክሴል ቫን ትሮትሰንበርግ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ መምከራቸውን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

አክሴል ቫን ትሮትሰንበርግ የኢትዮጵያ መንግሥት ችግሮቹን ለመፍታት በሚያደርገው ጥረት ላይ ተቋሙ እምነት እንዳለው ገልጸዋል።

የዓለም ባንክ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት በመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በማኅበራዊ ልማት፣በግብርና፣በቀጠናዊ ትስስር እና የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ለመደገፍ የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

የዓለም ባንክ በአይ.ዲ.ኤ 20 አማካኝነት ለዝቅተኛ አገራት 93 ነጥብ 5 ቢሊን ዶላር ውስጥ 66 ቢሊዮን ለ39 የአፍሪካ አገራት የመደበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለኢትዮጵያ 5 ነጥብ 7 ቢሊዮን ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ለመስጠት ቃል ገብቷል።

# የግብርና ምርቶች ላይ ብራንድ የመፍጠር ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል

ውብሸት ሰንደቁ




አዲስ አበባ፡- ስትራቴጂክ ተብለው በተለዩ የግብርና ምርቶች ላይ የብራንድ፣ እሴቶች እና መለያዎችን የመፍጠር ሥራ የሚቀጥል መሆኑን የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ገለፀ፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይዘሮ አያልሰው ወርቅነህ የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንች እና የጨንቻ አፕል ምርቶችን "ብራንድ" የሚደረጉበት የማስተዋወቅ መርሐ ግብር ከትናንት በስቲያ ሲካሄድ እንዳሉት፤ የብራንድ ምልክታቸው ከተዋወቀላቸው የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንች እና የጨንቻ አፕል በተጨማሪ ስትራቴጂክ ተብለው በተለዩ የግብርና ምርቶች ላይ የብራንድ፣ እሴቶች እና መለያዎች የመፍጠር ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ፡፡

ለምርቶቹ የተሠራው የብራንዲንግ ሥራ ምርቶቹ ሰፊ የገበያ መዳረሻ እንዲኖራቸው በማድረግ ለዓለም አቀፍ ገበያ እንዲቀርቡ ዕድሎችን ለመፍጠር እንደሚረዳ አመልክተው፤ ይህ የአምራቹን ኑሮ ከማሻሻሉም በተጨማሪ ሀገራዊ ጥቅም እንደሚያስገኝ ተናግረዋል፡፡

ብራንድ ያገኙት የግብርና ምርቶቹ በተደራጁ አርሶ አደሮች የሚለሙ መሆናቸውም ጠቁመው፤ በአርባ ምንጭ ሙዝን በማምረት የተሰማሩ 30 መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት 140 ሺህ 355 አባላት አላቸው፤ በጨንቻ አፕል በማምረት የተሰማሩ 12 መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት 242 ሺህ 906 አባላት የሚያሳትፉ ሲሆን በአዊ ድንች በማምረት የተሰማሩ 29 ኅብረት ሥራ ማህበራት ደግሞ 69 ሺህ 984 አባላት አካተው አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል ፡፡

የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንች እና የጨንቻ አፕል በዚህ መጠን እየተመረቱም ቢሆን ፈተናዎችን እያስተናገዱ ነው ያሉት ወይዘሮ አያልሰው፤ በሀገር አቀፍ ገበያ በስፋት ተደራሽ አለመሆን፣ ደካማ የግብይት ትስስር፣ በገበያ መሠረተ ልማት እጦት እና በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ጥቂት የሚባሉ ነጋዴዎችና ደላሎች እንዳሻቸው የዋጋ ተመን በማውጣት ገበያውን የሚቆጣጠሩበት የተዛባ የግብይት ሥርዓት መኖሩ አምራቹም ሆነ ሸማቹ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓቸው መቆየቱን አብራርተዋል፡፡

ችግሮቹን ለመፍታት ምርቶቹ በሚገኙበት ክልሎች ያሉ ኅብረት ሥራ ማኅበራትን የማጠናከር፣ ምርታማነትን የማሳደግ እና የምርቶቹን የግብይት ሥርዓት የማዘመን ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ዶክተር ሶፊያ ካሳ በበኩላቸው፤ የግብርና ምርቶች የብራንዲንግ ሥራ የግሉን ዘርፍ የኢኮኖሚ መሪነት ማረጋገጥ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ፖሊሲው አንዱ ግብ ነው ብለዋል።

ከውጭ ሀገራት የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካትና በሀገር ውስጥም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ምርት ማምረት ተገቢ መሆኑን ገልጸው፤ ከዚህ በፊት የሀገር ውስጥ ምርቶች ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን ጠብቀው ቢመረቱ እንኳን ብራንድ አለመዘጋጀቱ ችግር በመሆኑ የብራንዲንግ ሥራዎች አስፈላጊ ናቸው ብለዋል።

የግብርና ምርቶች ብራንዲንግ የገበያ ችግሮችን ለመቅረፍና የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ገበያዎችን ለማግኘት ዕድል ይሰጣል ሲሉም ገልፀዋል።

የምርቶቹ የብራንድ ስያሜዎች፣ አዳዲስ አርማዎች እና መሪ ቃሎች በይፋ እንዲተዋወቁ ከመደረጉም ሌላ ስለ ምርቶቹ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበዋል፡፡

በቅርቡ በተመሳሳይ ስትራቴጅክ ተብለው በተለዩ የግብርና ምርቶች ላይ የብራንድ፣ እሴቶች እና መለያዎች የመፍጠር ሥራ የሚቀጥል መሆኑን የገለፁት ዶክተር ሶፊያ፤ በመጪዎቹ ጊዜያት የሶማሌ ክልል ፍየል፣ የቤንሻንጉል ክልል ማንጎ ምርት እና የኦሮሚያ ክልል ቀይ ሽንኩርት የብራንድ ሥራ እንደሚከናወን ገልፀዋል፡፡

ዜና

# ከ25 ሺህ በላይ ቤቶች ለባለ ዕድለኞች ይተላለፋሉ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በዛሬው ዕለት 25 ሺህ 491 ቤቶች ለባለዕድለኞች በዕጣ እንደሚተላለፉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ አስታወቁ፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ከትላንት በስቲያ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ከ1997 ዓ.ም የ20/80 ተመዝጋቢዎች መካከል እስከባለፈው የካቲት 21 ድረስ ሳያቋርጡ ለ60 ወራት የቆጠቡ ቤት ፈላጊዎች ሙሉ ለሙሉ ቤት እንደሚያገኙ ገልጸዋል።

የ40/60 ተመዝጋቢዎች ከ40 በመቶ በላይ የቆጠቡ ተመዝጋቢዎች ንቁና ብቁ በመሆናቸው የዕጣ ሥነ ሥርዓቱ ውስጥ ተካተዋል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በጥቅሉ 79 ሺህ 794 ተመዝጋቢዎች በዕጣ አወጣጥ ውድድሩ ውስጥ እንደሚካተቱ ገልጸዋል፡፡

በ14ኛ ዙር ዕጣ አወጣጥ ሥነሥርዓት እድለኛ ለሚሆኑ ቆጣቢዎች አስቀድመው የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላለፉት ከንቲባዋ፤ በ1997 ዓ.ም የቤት ምዝገባ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች ተመዝግበዋል፤ በ2005 ዓ.ም በተካሄደው ዳግም ምዝገባ ደግሞ 700 ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ተመዝግበዋል ብለዋል፡፡ በ17 ዓመት ውስጥም 300 ሺህ የሚሆኑ ዜጎችን ማስተናገድ እንደተቻለ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ከንቲባዋ ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት 650 ሺህ የሚሆኑ ተመዝጋቢዎች ቤት እየተጠባበቁ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ 24 ሺህ የሚሆኑት የ1997 ዓ.ም ተመዝጋቢዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በአሁኑ ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ቤት ፈላጊ መሆናቸውን የተናገሩት ከንቲባዋ፤ በከተማዋ ወደ 54 ቢሊዮን ብር የሚሆን የመኖሪያ ቤቶች እዳ በመኖሩ ይህ ወደ ተበላሸ እዳ ተዛውራል ብለዋል፤ ባንኮች የዚህ ክፍያ ባልተጀመረበት ሁኔታ ለማበደር ዝግጁ ባለመሆናቸው ቤቶችን ለመጨረስ ችግር እንደነበርም ገልጸዋል፡፡


ፎቶ - ፋይል
ከንቲባ አዳነች አቤቤ

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፤ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የተረከቧቸው የ40/ 60 እና የ20/ 80 ቤቶች ቤቶች 139 ሺህ 8 ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ግንባታቸው ስላላለቀ ባይተላለፉም እንኳን 96 ሺህ ያህል ቤቶች ውሳኔ ያረፈባቸው፤ በ2011 ዓ.ም ለልማት ተነሺዎችና በምደባም ጭምር የተሰጡ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

# “ኢትዮጵያን ለማጽናት ሰው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መንግሥት ከፍተኛ ርብርብ እያደረጉ ነው። የንጹሐን ደምን በከንቱ የሚያፈስ ሸኔም ይሁን ሌላ አሸባሪ ኃይል በጀመርነው መንገድ ጉዟችንን አጠናክረን የምንቀጥል ከሆነ ዓላማቸውን ማክሸፍ ይቻላል።

ሸኔና ሌሎች የሽብር ቡድኖች የራሳቸው እግር የላቸውም፤ እግር የሚገጥምላቸው ሰው ሲያገኙ እሮጥ እያሉ ጥፋት ይፈጽማሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የራሳቸው ማሰቢያ ጭንቅላት የላቸውም፤ ታስቦ ሥራ ሲሰጣቸው ጥፋት ያካሂዳሉ፤ ንጹሐንን መግደል ምንም አይነት የፖለቲካ ዓላማን ሊያሳካ አይችልም፤ ንጹሐን ዜጎችን መጨፍጨፍ የሽብር ባህል ነው፤ ኢትዮጵያን ለማፍረስና ለመበተን የሚፈልጉ ኃይሎች መሻትን በገሀድ የሚያሳይ ነው ብለዋል።

መንግሥት የሕዝቦችን ሰላም ማስከበር ቀዳሚ ሥራው መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ ሕዝብም የመረጠውን መንግሥት የማድመጥና የማገዝ ቀዳሚ ተግባሩ መሆን አለበት።መንግሥት ፖሊሲ ሲቀርጽ፣ መረጃና ሀሳብ ሲሰጥ ሁሉም የሚያደምጥና የሚከተል ከሆነ ሁሉን ችግር ማስቀረት ይቻላል። ሁሉም ባለው ውስን መረጃና እውቀት ላይ ቆሞ አቅጣጫ የሚያሳይ በዝቷል፤ ይህ ወደፊትም የበለጠ ኪሳራ እንድናስተናግድ ያደርገናል። ከሳሽና ጠያቂ ብቻ ሳይሆን ኃላፊነት የሚወስድ ዜጋ መሆን እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

የጥፋት ኃይሎች ኢትዮጵያውያንን መግደል፣ ማጎሳቆልና ማሸበር ይችሉ ይሆናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከዋነኛው ዓላማችን ሊያስቀሩን ግን አይችሉም ብለዋል። በኢትዮጵያ የሚደረገው ግድያ መንግሥት ሥራውን ሳይሠራና ኃላፊነቱን ስለማይወጣ ተደርጎ የሚወሰደው ግን ስህተት ነው ሲሉም ተናግረዋል።

የዜጎቹን ሕይወት ለመታደግ መንግሥት 24 ሰዓት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤በዚህም በርካታ የንጹሐንን ሕይወት መታደግ ተችሏል ብለዋል። ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎች መኖራቸው እንዳለ ሆኖ በሚፈጠረው ችግር ሁሉ ሕይወታቸውን የሚገብሩ የጸጥታ አካላት እንዳሉ የጠቆሙት ዶክተር ዐቢይ፤ በቅርቡ እንኳን ደራሼ ላይ በነበረው ግጭት ከ80 ያላነሱ ፖሊሶችና አመራሮች መሞታቸውን ለአብነት አንስተዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ መንግሥት በየቀኑ የሕይወት መስዋዕትነት የሚከፍል ኃይል ነው። ወታደሮች፣ የክልል ልዩ ኃይሎች ሕይወታቸውን ገብረው ዜጎቻቸውን ለመታደግ ጥረት እያደረጉ ነው። በየቀኑ እየሞተ ሕይወት የሚታደገው ፖሊስ የተለየ ጥቅም ያለውም። ነገር ግን አገሩን ወዶና አክብሮ ሕይወቱን የሚከፍለው የጸጥታ አካላት ክብር ሊሰጠው እንደሚገባ ገልጸዋል።

# የፌዴራል መንግሥት በጀት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አቅጣጫዎችን ማብራሪያ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፤ የ2015 ዓ.ም የፌዴራል መንግሥት በጀት የዕዳ ክፍያ፤ የኑሮ ውድነቱን ማረጋጋት፣ ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ እንዲሁም የመልሶ ግንባታ እና ሰብዓዊ ዕርዳታ ላይ ያተኩራል ብለዋል።

በነጥቦቹ ላይ በዝርዝር ማብራሪያ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የዕዳ ቅነሳን አስመልክቶ ብድር መቀነስን ልክ እንደ ልማት መቁጠር አለብን ያሉ ሲሆን ባለፉት ዓመታት የነበረው የተከመረ ብድር መክፈል ካልቻለ ብዙ ጣጣዎች አሉት። ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በብድር መመለሻነት እስከመረከብ የሚያደርስ ስለሚሆን እና ሀገሪቷን ከሥጋት ነፃ ማድረግ ስለሚገባ የዚህ በጀት ዓመት አንዱ ትኩረት የብድር መጠንን መቀነስ ነው ሲሉ አስረድተዋል። በዚህ ዓመት 1 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ወይም 100 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ዕዳ ተከፍሏልም ብለዋል።

በሌላ በኩል የዋጋ ንረትን ማረጋጋት ሌላው የበጀት ዓመቱ ትኩረት እንደሆነ የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ባለፉት ሁለት፣ ሦስት ዓመታት ሳይቋረጥ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እያደገ በመሄዱ የዋጋ ንረት ሊከሰት እንደሚችል በመጠቆም የተከሰተውን የዋጋ ንረት ለመከላከል ከፍተኛ ሥራ ባይሠራ ኖሮ በነበረው ጦርነት፣ በኮሮና ወረርሽኝ እና አሁን ባለው የዩክሬንና ሩሲያ ጦርነት የዋጋ ንረቱ እጅግ የገዘፈ ሊሆን ይችል እንደነበር ተናግረዋል። ሆኖም ሙሉ በሙሉ ችግሩን መቅረፍ ባይቻልም የተደረጉ ከልምምድ የተገኙ ሥራዎች የኑሮ ውድነቱን በዚያ ልክ እንዳይሆን ማድረግ መቻላቸውንም ጠቁመዋል።

አሁንም የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች እየደረሰባቸው ያለውን ፈተና በተወሰነ ደረጃ ለማቃለል መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠበቅበታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከዚህ ውስጥ አንደኛው የገንዘብ አስተዳደርን በጥብቅ መቆጣጠር ነው ብለዋል። በተጨማሪም የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ አብራርተዋል። ግብርናን በማዘመን ገበያን የማረጋጋትና ሸጦ የመጠቀም ሁኔታ በበጀቱ አንድ አንኳር ጉዳይ ተደርጎ ይወሰዳል ሲሉ ተናግረዋል። የ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት በጀት 59 በመቶ ያህሉ ድህነት ቅነሳ ላይ እንደሚውል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልፀዋል።

የ2015 ዓ.ም የፌዴራል በጀት ትኩረት ያደርግባቸዋል ብለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካነሷቸው የትኩረት አቅጣጫዎች ሌላው ፕሮጀክቶችን ማጠናቀቅ ላይ የሚያተኩር ነው። ፕሮጀክቶች ያላግባብ የተራዘመ ጊዜ ሲወስዱ ኢኮኖሚውን በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ፕሮጀክቶች በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠሩ ገንዘቦችን ስለሚያንቀሳቅሱ ጊዜያቸው መራዘም እንደማይኖርበት ጠቅሰዋል።

በተመሳሳይ የፀደቀው በጀት ሌላኛው ትኩረት የመልሶ ግንባታ እና ሰብዓዊ ዕርዳታ መሆኑም ተገልጿል። የተፈናቀሉ የተጎዱ ሰዎችን መልሶ ማቋቋምና መርዳት አቅም በፈቀደ መሠረት በመንግሥትም ሆነ በሁሉም ሀብት ወደ ቀደመ ሕይወታቸው እንዲመለሱ ማድረግ የበጀቱ ትኩረት መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል። የሀገር ደህንነት እና ሰላምን ማስጠበቅ በትኩረት እንደሚሠራ አያይዘው ገልፀዋል።

የ2014 በጀት ዓመት የመንግሥት ገቢን በተመለከተም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለምክር ቤቱ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በበጀት ዓመቱ በ11 ወራት ውስጥ መንግሥት 330 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ አቅዶ 309 ቢሊዮን ብር ማግኘቱን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል። ይህ ገቢ ከአለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ50 ቢሊዮን ብር ጭማሪ አለው። ገቢው ብዙ ቦታ ባለው የንግድ ሥርዓት መዛባት ምክንያት በገቢና ወጪ ንግዶች ላይ ጫና ተፈጥሮ እና በግጭት ቀጠና ውስጥ ያሉ ገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶችና ቢሮዎች በተዘጉበት ሁኔታ በመሆኑ ሊመሠገን የሚገባው መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለው ገልፀዋል።

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ ያለውን የመንግሥት ወጪ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በ11 ወራት ውስጥ 500 ቢሊዮን ዶላር ገደማ መውጣቱን ተናግረዋል። የወጣው ወጪ ከገቢው ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ የተለያዩ ሥራዎችን እንደሚጠይቅ ጠቁመዋል።

ሆኖም ኤክስፖርት ላይ የመጣው እመርታ በጣም ግዙፍ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስተዋል። ይህንን የኤክስፖርት ዕድገት ማስቀጠል ከተቻለ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የንግድ መዛባትና የውጪ ምንዛሪ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ይስተካከላል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከ2002 እስከ 2012 ዓ.ም ባሉት ዓመታት 3 ቢሊዮን የኤክስፖርት ምጣኔ ለመድረስ ስትንገዳገድ ነበር ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በነበሩት አሥር ዓመታት ውስጥ የነበረው የኤክስፖርት ዕድገት 1 ቢሊዮን ዶላር ገደማ ጭማሪ እንደታየ በማንፀር ባለፈው ዓመትና በዘንድሮው ዓመት በተሠራው ሪፎርም በሸቀጦችና አገልግሎቶች ኤክስፖርት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ እንደተገኘ ገልፀዋል።

በኤክስፖርት የተገኘው ውጤት የሪፎርሙን ስኬት የሚያሳይ እና እጅግ ተስፋ ሰጪ ጅማሮ መሆኑን ያመላከተ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግብርና ከተገኘው የኤክስፖርት ዕድገት ወደ 25 በመቶ የሚጠጋውን ዕድገት ማምጣት ችሏል ብለዋል። ኢትዮጵያ በዘንድሮው ዓመት በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር ቡና ኤክስፖርት ማድረጓንም አስታውሰዋል።

የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ላይም ኢትዮጵያ ውስጥ መከራ እየተወራም ቢሆን ከሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ኢትዮጵያ ውስጥ መሳብ መቻሉን አንስተዋል።

ፋይናንሽያል ሴክተሩ በእጅጉ እያደገ መሆኑንም አክለው ገልፀዋል። ከሪፎርም በኋላ የፋይናንስ ሴክተሩ መነቃቃት አሳይቷል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ የባንኮች አጠቃላይ ሀብት 2 ነጥብ 3 ትሪሊየን ብር መድረሱንና የቅርንጫፍ ቁጥራቸውም 8 ሺህ 242 መድረሱን አብራርተዋል። የባንክ ደብተር ካላቸው ሰዎች በባንክ የተቀመጠው ገንዘብ 1 ነጥብ 6 ትሪሊየን ብር መድረሱንም አክለው ገልፀዋል።

የተፈጠረውን የበጀት ጉድለት ለማሟላት የመፍትሔ ርምጃዎች እንደሚወሰዱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልፀዋል። የበጀት ጉድለትን ከብሔራዊ ባንክ በመበደር ልናሟላ ከሞከርን የኑሮ ውድነቱን ያባብሰዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ የበጀት ጉድለትን ማሟላት እንደመፍትሔ እንደሚወሰድ ተናግረዋል።

# “ኢትዮጵያ ወደ ዳገት ስምታደርገው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከባድ፣ ከፍተኛ ጉልበት፣ ትጋትና ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ ተባብሮ ወደፊት መግፋት ይጠበቃል፡፡

በአንፃሩ ወደ ኋላ መመለስ በጣም ሩቅ እንደመሆኑ መጠን ቀላልና ብዙ ጉልበት እንዲሁም ትብብር እንደሚያስፈልግ አንስተው፣ ሁሉም ሥራውን ሳይሠራ ቢተኛ በአንድ ጊዜ ወደ ኋላ የሚመለስ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በመሆኑም የተከበረው ምክር ቤትና ሀገር የሚወድ ዜጋ የኢትዮጵያ የዳገት ጉዞ ተጨማሪ ጥረትና ትጋት ስለሚጠይቅ በተቻለ አቅም ወደላይ እንድትወጣ መደገፍና ጉልበት መሆን ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ይህን ማድረግ የማይችልና አቅም የጎደለው እንዲሁም ስሜት የሚያሸንፈው አካል ካለ ደግሞ በትንሹ ሀገር ወደ ቁልቁለት ጉዞ እንዳትንሸራተት መደገፍ የሚያስፈልግ መሆኑን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያን ወደ ኋላ በሚጎትት ተግባር ላይ መሳተፍ ግን የጠላቶቻችንን ፍላጎት ማሳካት በመሆኑ እንዲህ ባሉ ተግባራት ውስጥ መሳተፍ አስፈላጊ እንዳልሆነ በማብራሪያቸው አመልክተዋል፡፡

ጠላቶቻችን በዘር፣ በእምነት እንዲሁም በልዩነቶቻችን በመጠቀም እንድንፈርስ የሚያሴሩት ተግባር በርካታ በመሆኑ ሀገር የሚወድ ዜጋ ሁሉ ይህን ተግባር መደገፍ የለበትም ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ ውስጥ የሰላም እጦት፣ ግጭት፣ ግድያና ሌሎች ወደ ኋላ የሚጎትቱ ፈተናዎች ቢኖሩም ይህን ሁኔታ በትዕግስት በማለፍ ኢትዮጵያን ወደ ፊት ማሻገር በሚገባው ሁሉ መሳተፍ ተገቢ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በበርካታ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ የሀገራት ባንዳዎች ሀገርን በሚያፈርሱ ተግባራት ውስጥ በመሳተፋቸው ያተረፉት ነገር ቢኖር ፀፀትና መከራ መሆኑን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያም ወደዛ መከራ ብትሄድ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሳተፉ አካላት እዳው ገብስ ነው በማለት ተቋሞቻቸውን ዘግተው እንደሚወጡ መታወቅ ይኖርበታል ብለዋል፡፡

በመሆኑም የኢትዮጵያ ጠላቶች እንደ ተኩላ መሆናቸውን ለተከበረው ምክር ቤት ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ተኩላ የበግ መንጋ እርስ በእርሱ እንዲጠራጠር በማድረግ በማዳከምና በማጋጨት በበጎች መካከል ያለውን ኃይል መቆጣጠር እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታም ሕዝቦች ከተለያዩ፣ እርስ በእርሳቸው ከተጠራጠሩና ከተጋጩ በቀላሉ መቆጣጠር ይቻላል በማለት ጠላት የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ከዚህ መሰል የተኩላ አይነት እንቅስቃሴ መጠንቀቅ ተገቢ መሆኑን ለምክር ቤቱ አንስተዋል፡፡

ሰው ከጎረቤቱና ከተዋለደው ወንድሙ ጋር ጠላት ነኝ ብሎ የሚያስብ ከሆነ ሩቅ ካለው አካባቢ ጋር ዘመድ ሊሆን የማይችል በመሆኑ በዚህ ረገድ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉና እርስ በእርሳቸው ቅርበት ያላቸው አካባቢዎች መካከል ሰላም የሚያስፈልግ በመሆኑና ሰላም ሆኖ ለማደር ቅድሚያ ከጎረቤት ጋር በሰላም አብሮ ማደር ወሳኝነት እንዳለው አብራርተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሀገር አንድነት ጋር በተያያዘ ለምክር ቤቱ ባቀረቡት ማብራሪያ አንድነት ማለት ብልጽግና፣ ምቾትና የተደላደለ ነገር ባለበት ወቅት አንድ መሆን ማለት ብቻ ሳይሆን አስቸጋሪ በሆነ ወቅትና መለያየት ቅርብ በሆነበት ወቅትም አንድ ለመሆን መወሰን ትልቅነት በመሆኑ በችግርና በመከራ ወቅት በጋራ በመቆም ሀገር ማሻገር፣ ኃላፊነት መውሰድ እንዲሁም ለሀገር አንድነት ሲባል ለመስዋዕትነት ዝግጁ መሆንንም ያካትታል ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## «ቢቻል ወደ ፊት መግፋት ፤ ባይቻል ወደ ኋላ መመለስ እንዳይኖር ታኮ ማድረግ ... »

በምርጫ ወደ ስልጣን የሚመጣ መንግሥት ሁል ጊዜም ቢሆን አቅሙ ሕዝብ ነው ። ሕዝብ አምኖ ይሆነኛል ብሎ እንደመረጠው ሁሉ የማስፈጸም አቅሙም ከእያንዳንዱ የሕዝብ ተሳትፎ የሚመነጭ እና በዚሁ የሚሰላ ነው ። ከዚህም የተነሳ ሕዝብ የመረጠውን መንግሥት የመጠየቅ መብት እንዳለው ሁሉ የማገዝም ከፍ ያለ ኃላፊነት አለበት።

በተለይም በሕዝባዊ የለውጥ መሻት ወደ ስልጣን የመጣ መንግሥት፤ የሕዝብን የለውጥ መሻት እውን ለማድረግ ከሁሉም በላይ የሕዝብን ቀጥተኛ ተሳትፎ ይጠይቃል። ያለ ሕዝብ ተሳትፎ መንግሥት የሚሄድባቸው የለውጥ መንገዶች በተግዳሮት የተሞሉ ከመሆናቸውም በላይ ፤የለውጥ ኃይሉን ሆነ የለውጡ ባለቤት /ሕዝቡ/ ያልተገቡ ዋጋዎችን እንዲከፍል ያስገድዷቸዋል ።

በለውጥ ወቅት በተቋማት ውስጥ ከሚከሰቱ ግራ ማጋባቶችና ትርምሶች ጀምሮ፣ ተቋማቱ ይዘዋቸው የመጡት አጋች ቢሮክራቲክ አመለካከቶችና አመለካከቶቹ የሚወልዷቸው ፈተናዎች ለለውጡ ትልቅ ተግዳሮት መሆናቸው የማይቀር ነው ። ይህንን ተግዳሮት በጽናት አሸንፎ ለመሻገር ከሁሉም በላይ የሕዝብ ተሳትፎ ወሳኝ ነው።

የሕዝብ ንቁ ተሳትፎ በተቋማት ውስጥ ያሉ ለውጡን የሚገዳደሩ አስተሳሰቦችን በግልፅ ከመታገል ጀምሮ፣ ራስን የለውጥ ኃይል አድርጎ አዲሱን የለውጥ አስተሳሰብ አሸንፎ እንዲወጣና በቢሮክራሲው ውስጥ ገዥ ስፍራ እንዲይዝ የማይተካ ሚና አለው። ይህንን ሚናውን ያልተረዳ ሕዝብ የለውጥ እሳት በማንደድ ብቻ ለውጡን ስኬታማ ማድረግ አይችልም።

በተለይም እንደኛ ባሉ ውስብስብ የታሪክ ምዕራፎችን አልፈው፣ እጅግ በበዙ ፈተናዎች ተከበው በለውጥ ሂደት ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች፣ ብዙ ዋጋ የከፈሉለትን ለውጥ ለመንግሥት አሳልፈው በመስጠት ስኬታማነቱን እጃቸውን አጣምረው የመጠበቃቸው እውነታ ባልተገባ መዘናጋት ተጨማሪ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ አትራፊ የሚያደርጋቸው አይደለም።

ለውጡ መንገጫገጭ ባጋጠመው ቁጥር ጣትን በመንግሥት ላይ መቀሰርና ራስን ሁል ጊዜ ከተጠያቂነት የማግለል አካሄድ ለውጡ በጀመረው ርምጃ እንዳይጓዝ ከማድረጉም ባሻገር በለውጡ ኃይል ላይ ሊፈጥር የሚችለው ጫና የለውጥ ስሜት መቀዛቀዝ መፍጠሩ የማይቀር ነው።

በሀገራችን ሕዝብ የለውጥ ኃይል ስለመሆኑ ከቀደመው ዘመን ጀምሮ በስፋት ተሰብኳል ፤ በስፋትም ተጽፏል። በዚሁ ልክ የሕዝቡ የለውጥ ተሳትፎ ሞቅታ ከሚፈጥረው የስሜት መጋጋል ባለፈ ስትራቴጂክ በሆነ መልኩ ለውጡን በተቀናጀና በተናበበ መልኩ ለስኬት ማብቃት በሚያስችል መልኩ የተሳሰረና የተናበበ አይደለም ።

ከዚህ የተነሳም ለውጡ ከስሜት ግለት ወጥቶ ወደ ተጨባጭ የታሪክ ጉዞው ሲገባና መንገጫገጮች ሲያጋጥሙት የሚሰሙት ጩኸቶች በሙሉ መንግሥትን የችግሮች ሁሉ ባለቤት የማድረግና የመክሰስ ባህሪ የተላበሱ ናቸው። ይህም ራስን ከለውጡ ዋንኛ ኃይልነት የማግለልና ለችግሮች ተጠያቂ የመፈለግ አዝማሚያ ለውጡን አቅመ ቢስ ማድረጉ አይቀርም።

የለውጥ ኃይሉ የመንግሥት ስልጣን ይዞ እየተንቀሳቀሰ ያለው በለውጡ ቀምር በተሰላ የአመራር ብቃትና ርዕይ ሕዝቡን ለማሻገር ነው። የሚሻገር ሕዝብ ደግሞ ከቆመበት መሄድ እንደሚያስፈልገው ፤ በመንገድ ተግዳሮት እንደሚያጋጥመው፤ተግዳሮቱን ማሸነፍ የሚያስችል የስነልቦና ዝግጁነት መፍጠር እና ለዚህ ሁሉ ራሱን ያዘጋጀ መሆን አለበት ።

ችግር ባጋጠመውና በችግሮች በተፈተነ ቁጥር የቀደመውን ዘመን መናፈቅ፣ ለተፈጠሩ ችግሮች ሁሉ ራሱን ከተጠያቂነት ማራቅ፣ ለችግሮች እራስን መፍትሔ አድርጎ አለማሰብ ፣ ተፈጥሯዊ በሆነው የለውጥ ጎዳና ውስጥ በሚያጋጥሙ የተለያዩ መንገጫገጮች ቶሎ መፈታትና መቆዘም በለውጥ ጎዳና ቆሞ ቀር ያደርጋል።

ከዚህ አንጻር ሕዝባችን የደም ዋጋ ከፍሎ ያመጣው ለውጥ ስኬታማ እንዲሆን ለችግሮች ሁሉ ባለቤት ከመፈለግ ወጥቶ የለውጥ ኃይል መሆኑን በተጨባጭ በሚያሳይ ቁርጠኝነት ከለውጥ ኃይሉ ጋር ተናቦ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል። በለውጡ ዋዜማም ሆነ መባቻ የነበረውን የለውጥ መንፈስ ግለት ማደስ ይኖርበታል ።

ለለውጡ ስኬት የሕዝቡ ያልተገደበ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። በተለይም አሁን ለውጡ እየተፈተነበት ባለበት የጸጥታና የመልካም አስተዳደር ችግር ዘላቂ መፍትሔ ለማፈላለግ የሕዝቡ ንቁ ተሳትፎ መተኪያ የለውም። በአሸባሪዎች የሚገደሉትን ዜጎች ለመታደግ የመንግሥት ጥረት በሕዝብ ተሳትፎ ሊደገፍ ይገባል ። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ችግሩ በዘላቂነት ሊፈታ አይችልም።

ከዚህ ውጪ በለውጥ ወቅት በሚጋጥሙ መንገጫገጮች የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚደረጉ ጥረቶች ሀገርና ሕዝብን ዋጋ ሊያስከፍሉ ይችላሉ እንጂ የተጀመረውን ለውጥ የማስቆም አቅም አይኖራቸውም። ይህን በጊዜ ተረግቶ አሰላለፍን ለማስተካከል አሁንም ጊዜ አለ። ይህን አለማድረግ የታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ባለፈ ፤ በራስ ላይ ጸጸት የማከማቸት መታወር ነው ።

ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አሕመድ ትናንት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት እንዳሉት ፤ “ ሀገር አሁን አጭር በሆነው ወሳኝ የዳገት መንገድ ላይ ነች። ቢቻል ወደ ፊት መግፋት፤ ባይቻል ወደ ኋላ መመለስ እንዳይኖር ታኮ ማድረግ ያስፈልጋል”። ይህ ደግሞ ከለውጥ ኃይሉ ብቻ ሳይሆን ከየትኛውም ለሀገር በጎ አሳቢ ዜጋ የሚጠበቅ ነው። ከዚህ ውጪ የትኛውም ኃይል ሀገርን ወደ ኋላ /ወደ ቁልቁለቱ/ ለመጎተት ከሚደረግ ጥረት መቆጠብ ይጠበቅበታል። በዚህ ተግባሩ የለውጡን ጉዞ ሊያስቆም አይችልም ። የሚያተርፈው የታሪክ ተወቃሽነትና ጸጸት ብቻ ነው።

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ምክክራችን እንዲሰምርልን

**ታምራት ተስፋዬ**

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን፣‹‹የአስተሳሰብ ልዩነት ፣ፉክክርና የሚጋጭ ፍላጎት (Conficting Interest) ባለባቸው አገራት ውስጥ ችግሮች በአንድ ፓርቲ ፣በአንድ ቡድን ወይንም በጥቂት ሰዎች አይፈቱም።ጥቂቶች በር ዘግተው ቢጨነቁና ቢጠበቡም መፍትሄ ሊሆኑና ሊያመጡም ፈፅሞ አይቻላቸውም። በመሆኑም ልዩነቶችን ለማጥበብ ሆነ ለማስታረቅ፣ ከተናጠል ይልቅ የጋራ ውይይት ባህልና ልምድ የግድ ነው››ይላሉ።

በተለይ በግሎባላይዜሽን ዘመን ከአግላይ Exclusive ይልቅ አሳታፊ Inclusive መሆን የግድ እንደሚልና አንደኛው ሌላውን ከሚያገል ጠባብ አስተሳሰብ ነፃ ወጥቶ‹‹የጋራ ውሳኔያችን ትክክል ነው፣አንድ ስንሆን እንጂ ስንለያይ በቀላሉ እንወድቃለን‹‹Divided we fail United we Stand››ወደ ሚል መርህ መምጣት እንደሚያስፈልግም ያሰምሩበታል።

ኢትዮጵያ በየዘመኑ የተፈጠሩና ከዘመን ዘመን እየተሸጋገሩ የመጡ ያልተቋጩ ሃሳቦች፣በይደር የቆዩ አለመግባባቶች እንዲሁም አገር ትቀጥል ዘንድ ቅድሚያ ተነስቷቸው የቆዩ የማያግባቡ አጀንዳዎች የተሸከመች አገር ናት።አገሪቱ ልዩነቶችን በውይይት የመፍታት የአሳታፊነት ባህልና ልምድ የሌለባት መሆኑ ደግሞ ችግሮች በቀላሉ ፈጣን ምላሽ እንዳያገኙ፣ውስጥ ውስጡን እንዲብላሉና ከትላንት እስከ ዛሬ እንዲከተላት ምክንያት መሆኑ በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል።

‹‹እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ››እኔ የማስበው ሁሌም ትክክል ነው››የሚል የአመለካከትና የባህሪ ችግርም ረጅም ጊዜ ሲያደክም ከርሟል።‹‹ችግር ካለም እኛው የስርአቱ ባለቤቶች እንናገር እንጂ ሌላው ምን ቆርጦትና ምንስ አግብቶት ነው በስርአቱ ላይ ትችት የሚሰነዝረው?››የሚለው ከእኔ እና ከእኛ ውጭ ላሳር አመለካከትና ተግባርም ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን በሁሉ ረገድ ሊቀይሩ የሚችሉ የተለያዩ ገንቢ አስተያየቶችና መፍትሄዎች ሳይቀር ከስመው እንዲቀሩ ምክንያት ሲሆን ታይቷል።

ትላንትም ሆነ ዛሬ እየተመላለሰ የሚደቁሰንና አዙሪት ሆኖብን ወደፊት አላንቀሳቅስ ያለን ችግራችንን ተነጋግረንና ተወያይተን ፍቱን የሆነ መፍትሄ ማስቀመጥ አለመቻላችን ነው። አጀንዳችን መጋጨት እንጂ መግባባት አይደለም።ለውጥ በአንድነት እንጂ በመለያየት እውን አይሆንም።ለውጥ ትናንትን ገድሎ፣ ዛሬን ብቻ አንጠልጥሎም አይሳካም።

ይሑንና ከህልውና ባሻገር ስለ አንድ አገር ስለመፅናትና መቀጠል እንዲሁም ስለ ሁለንተናዊ እድገት ሲታሰብ ለዚህ ስንክሳር መፍትሄ መስጠት የግድ ይላል።ኢትዮጵያ አንድነቷ ተረጋግጦ፣ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖ የህዝቧን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎት ማርካት የምትችለው በአንድ በኩል ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ሲኖራት ነው። ይህ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ምን አይነት ቅርጽ መያዝ አለበት? ምን አይነት የዲሞክራሲ፣የፖለቲካ፣ የህግ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ተቋሞች ያስፈልጉናል የሚሉ ትልልቅ አገራዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ደግሞ በጠረጴዛ ዙሪያ ሊመከርበት ይገባል።

ለበርካታ አመታት በተለይ ባለፉት አራት አስርት አመታት የውይይት እሳቤ በኢትዮጵያ ምድር እውን ይሆን ዘንድ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ከተለያዩ አካላት ሲነሳ ቆይቷል።‹‹ይሁን››የሚል መልስ የሰጠ መንግስት ግን አልነበረም። በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የሚመራው መንግስት በአንጻሩ ይሕን ታሪክ ለመለወጥ በተለይ ስለ ኢትዮጵያ ቁጭ ብሎ ለመምከር በሩን ክፍት አድርጓል።ውይይቱ እውን ይሆን ዘንድ በሁሉ ረገድ ፈቃደኛ መሆኑን የሚያመላክት እርምጃዎችን እየተራመደ ይገኛል።

ፈፅሞ ሊቀራረቡና ሊታረቁ አይችሉም የተባሉ ሃሳቦችና ከግለሰብ አንስቶ እስከ አገራት የተቀራረቡት እንዲሁም ከልዩነት ይልቅ በአንድነት ለጋራ አላማ የተሰለፉት በምክክር ነው።ደቡብ ኮሪያ ለዚህ እሳቤ ጥሩ ምሳሌ ናት። ደቡብ ኮርያውያን ዛሬ ላይ በብልፅግና ጎዳና የመራመዳቸው ዋነኛው ምክንያት ከአምስት አስርት አመታት በፊት ከሁሉ በላይ ለውይይት ቅድሚያ መስጠታቸው እንደሆነም ታሪክ አሳይቶናል።

በአካታች አገራዊ ምክክሩ ኢትዮጵያ ታተርፋለች እንጂ አትከስርም።ከሌሎች አገራት አንፃር ሲታይም የኢትዮጵያ አብዛኞቹ ችግሮች በውይይት ፈር ሊይዙ የሚችሉ ናቸው።የምክክር መድረኩ ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ለዘላቂ ሰላም፣ ለተሻለ የፖለቲካ ባህል ግንባታና ለሁለንተናዊ እድገትም እጅግ ወሳኝ ነው።

የወደፊቷ ኢትዮጵያ ምን መምሰል አለባት የሚለው ላይ ግልፅ አቅጣጫን ያስቀምጣል።የተረጋጋችና በኢኮኖሚ የዳበረች ዲሞክራሲያዊት አገር ለመፍጠር እጅግ ወሳኝ ነው።ይሑንና ምክክሩ እንዴት ውጤታማ ሊሆን ይችላል ከማንስ ምን ይጠበቃል የሚለው ወሳኝ ጥያቄ ነው።

የተለያዩ የስነ ልቦናም ሆነ የፖለቲካ ምሁራንም አንድን ውይይት ምክክር ውጤታማ ለማድረግ ይረዳሉ የሚባሉ መሰረታዊ ነጥቦችን ሲያስቀምጡ፣ ከወገናዊነት ነፃ በመሆን ሚዛናዊ አስተሳሰብን ማራመድ፣ሁሉም እኩል የሚያሸንፍበት/ Win-Win Resolution/መንገድ መከተል፣ግልጸኝነት፣ ትዕግስት፣ መደማመጥ እና የሌሎችን ሀሳብ ማክበር የግድ እንደሚል አፅንኦት ይሰጡታል።

በውይይት በምክክር ወቅት በሰዎች መካከል የአመለካከት ልዩነት ሊፈጠር ይችላል።የሃሳብ ልዩነቶች ደግሞ አላማንና ግብን የማያስቱ እስከሆነ ድረስ ተፈጥሯዊ ሰውኛ /Humanistic/ ናቸው።የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ ለመቀጠል ከሁሉም በላይ ውይይትን ውጤታማ ለማድረግ ግን በተለይ የሰጥቶ መቀበል መርህ እጅግ ወሳኝ ነው።

ሚዛናዊ ሆኖ የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥ የራስንም ለሌሎች ለማስረዳት መዘጋጀት ይገባል። አንድ ጥግ ይዞን የሌሎችን ሀሳብ በጥርጣሬ መመልከት ለስህተት ይዳርጋል።ይልቁንም የሀሳብ ልዩነቶችን በቅንነት በመመልከት ሌላው የሚያስበውን በሌላው ጫማ ውስጥ ሆኖ ማየትን የሚጠይቅ ነው ።

አገራዊ የምክክር መድረኩ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ ከሁሉ በላይ በሁሉ ረገድ አካታች መሆን ይኖርበታል። ስለኢትዮጵያ ያገባኛል፣ ይመለከተኛል ወይም ደግሞ ጥያቄ አለኝ የሚሉን በትምህርት ደረጃ፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በፖለቲካ አመለካከትና በጾታ ሳይገደቡ ማሳተፍና ሃሳቦችን መውሰድ ለውይይቱ ፍሬያማነት ትልቅ ጠቀሜታ አለው። የተለያዩ ሃሳቦች ሊነሱ ቢችሉም ለምክክሩ የሚቀረጹት አጀንዳዎች በዋናነት ኢትዮጵያን ማዕከል ያደረጉና ዘላቂ ሠላምን የሚያመጡ መሆን ይኖርባቸዋል።

ለአገራዊ ምክክሩ ውጤታማነት ከሁሉ በላይ ከግልና ከቡድን ይልቅ የአገርና የሕዝብን ጥቅም ማስቀደም የግድ ይላል። በዚህ ረገድ በተለይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። የአገር ህልውና የገዢ ፓርቲ አሊያም የአንድ ፓርቲ ጉዳይ አይደለም።እንደ ዜጋ ወይም እንደ ፓርቲ መንቀሳቀስ የሚቻለውም አገር ስትኖር ብቻ ነው።የአገርን አንድነት የሚጠብቁና የአገርን ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ደግሞ የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ልዩነት ሊኖረው አይገባም።

ለምክክሩ ውጤታማነት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የምሁራን ሚና የላቀ ነው።በተለያዩ አገራት የተካሄዱ አገራዊ ምክክሮች ውጤታማ እንዲሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የማይተካ ሚና ተጫውተዋል።እንደአገር ሳያግባቡ የቆዩ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በመለየትና የሚፈቱበትን መንገድ በማመላከት ውይይቶቹ ለውጤት እንዲበቁ ማድረግ ችለዋል።ይህን መንገድ የአገራችን ምሁራንም ሊራመዱበት ይገባል።መገናኛ ብዙሃኑ መድረኩን የሚዘግቡበት መንገድ በራሱ በጥንቃቄና በአግባቡ ሊቃኝና ከወዲሁ ተገቢው ዝግጅት ሊደረግበት የሚገባው ነው።

አንድ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ቢኖር አገራዊ የውይይት መድረኮች ሲካሄዱ ሁሉም ጥያቄ ፈጣን መልስ ይኖረዋል ብሎ ማሰብም አግባብ አለመሆኑ ነው።የእያንዳንዱ ምክክር መልስ የሂደት ውጤት መሆኑን ጠንቅቆ መገንዘብ ያስፈልጋል። ‹‹ጥያቄው ላይ ዛሬ ተወያይተናል መልሱን ዛሬ ካልሆነም ነገ እንፈልጋለን››ብሎ ማሰብም ግዙፍ ስህተት መሆኑን መረዳት ይገባል።

በአጠቃላይ አገራዊ ምክክሩ እንደሌሎች የውይይት መድረኮች ተድበስብሶ የሚቀር ሳይሆን የሚዳሰስ ውጤት ማምጣት በሚቻልበት መልክ ሊቃኝ ይገባል።ለዓመታት ስንጠይቅ የመጣን ከመሆናችን አንፃር በጣም በጥንቃቄና በጥሩ ዝግጅት መካሔድ ይኖርበታል።ለዚህ እጅግ ወሳኝ ታሪካዊ ሁነት ሁለንተናዊ መሳካትም ሁሉም የበኩሉን መወጣት የነገ ሳይሆን የዛሬ ተግባሩ መሆን አለበት።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# «ጥላቻን ይዞ የተወለደ የለም... »

ከምዕራብ ወለጋውና ከጋምቤላው የንጹሐን ጭፍጨፋ በቅጡ ሳናገግም በቄለም ወለጋ አሸባሪው ሸኔ ተመሳሳይ ጭፍጨፋ መፈጸሙን ተረዳን። ያሳዝናል። መንግሥት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥና አሸባሪዎችን ለመደምሰስ ከሚያደርገው ዘመቻ ጎን ለጎን ከዚህ አዙሪት በዘላቂነት ሰብሮ ለመውጣት የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ግድ ይላል። እንደ አገራዊ ምክክሩ ያሉ ተግባራት እንዲሳኩ ሁለንተናዊ ድጋፍ ከማድረግ ባሻገር የአመለካከት ለውጥ ላይ አበክሮ መሥራት ይጠይቃል። ለዚህ አብነት ቢሆን በሚል መጣጥፌን ይዤ ተመልሻለሁ።

የዛሬዎቹ የዓለማችን ፍርድ ቤቶች፣ ችሎቶች የበርካታ ሺ አመታት ሒደታዊ ለውጥ ውጤት ናቸው። የሕግ ታሪክ ከየትነት ከባቢሎን እስከ ፋርስ፣ ከግሪክ እስከ ሮማ፣ ከአውሮፓ እስከ ፈረንሳይ፣ ከግብፅ እስከ ኢትዮጵያ ያካለለ ነው። ከታላቁ መፅሐፍ ፣ ከቅዱስ ቁራን፣ ከባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ ዳኝነቶች ተቀድቶ የተቀመረ ነው። በአገራችንም የመጀመሪያው ሕገ መንግሥት እስከረቀቀበት 1923 ዓ.ም ፣ በእንግሊዝ እገዛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እስከተሰየሙበት፣ የፍትሐብሔርና የወንጀል ሕጎችን ከፈረንሳይና ሌሎች አገራት አምጥተን እስክናነብር በፍትሐ ነገስትና በባህላዊ ሽምግልና ነበር የምንዳኘው። ዘመናዊ ትምህርት፣ የአየር መንገድ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የባንክ፣ የአውራ ጎዳና፣ ወዘተ. ድርጅቶች ቀደምት መሥራቾች የውጭ አገር ዜጎች እንደነበሩት ሁሉ የአገራችን ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት እንግሊዛዊ እንደነበር ይወሳል።

በፍርድ ቤቶች ፍትሕ ሲከበርም፣ ሲዛባም፣ ሲጓደልም አጋጥሞን ያውቃል። በችሎት አዳራሽ የበዳይና የተበዳይ ወገኖች ለጠብ ሲገባበዙ፣ አንዱ በሌላው ላይ ከንፈሩን ሲነክስ፣ አይኑን ሲያጉረጠርጥ አይተናል። የሟች ወገኖች በፍርድ ቤቱ ውሳኔ ተደስተው ችሎቱን በእልልታ ሲያቀልጡት በተቃራኒው የገዳይ ወገኖች ችሎቱን በዋይታ ሲያደባልቁት ታዝበናል። ተከሳሾች በማዕከላዊ፣ በፖሊስ ጣቢያ በምርመራ ስም የተፈፀማበቸውን ግፍ፣ ስቃይ ልብሳቸውን ሱሪያቸውን አውልቀው ሰንበራቸውን፣ የተንኮላሸ ብልታቸውን ለችሎቱ ሲያሳዩ የተበዳይ ወገኖችና ታዛቢዎች በእንባ ሲራጩ ተመልክተናል።

ተጠርጣሪዎች ስማቸው ሲጠራ አቤት ባለማለት ከመቀመጫቸው ባለመነሳት ችሎቱን ወይም ዳኞቹን ገለልተኛ አይደለህም ብለው ሲቃወሙ አይተናል። የዳኝነት ሥርዓቱን ነፃነት ሲሞግቱ ታዝበናል። አንዳንድ ወገኖች ከችሎት አደባባይ የተነፈጉትን ፍትሕ በእጃቸው ሊቀዳጁ ሲሞክሩ፣ ሌሎች ፍትሕን ከችሎት አደባባይ በላይ ከፈጣሪ ሲለማመኑ ተመልክተናል። በአገራችን ከጥቂት አመታት በፊት በሀዋሳ በአንድ ጠበቃ ላይ ከተፈፀመ ግድያ በቀር የተለመደ ባይሆንም በኮሎምቢያ፣ በሜክሲኮ፣ በኤልሳቫዶር እና በሌሎች አገራት ጠበቆች፣ ዳኞች ሲታገቱ፣ ሲገደሉ ከቴሌቪዥን መስኮት አይተናል። በፈጠራው ዓለም ችሎትም በዊሊያም ሼክስፔየር «የቬኑስ ነጋዴ» ሻይሎክ ከአራጣ ተበዳሪው መቀመጫ ሙዳ ስጋ ለመቁረጥ ሲቋምጥ አንብበናል።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ጥቅምት 4 ቀን 2019 በዩናይትድ ስቴትስ ዳላስ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች በአንዱ የሆነው ግን በአግራሞት፣ በአድናቆት እጅን በአፍ ያስጫነ ፣ ታዳሚውን ፣ ተከሳሹን ፣ ዳኛዋን ሳይቀር በእንባ ያራጨ፤ በቴሌቪዥን፣ በዩቲዩብ የተመለከቱትን ሚሊዮኖችን ሳይቀር ያስለቀሰ ፣ የይቅርታን ጥጋ ያመላከተ ነበር። የሟች ታናሽ ወንድም ቦታም ጅን ከተቀመጠበት የምስክር ሳጥን ድንገት ልብን በሚሰብር ድምፅ እንባ ያቀረሩ አይኖቹን ወደ ዕለቱ ዳኛ ወርውሮ በዚያ ችሎትም ሆነ በሌሎች ፍርድ ቤቶች ተጠይቆ የማያውቅ እንግዳ ጥያቄ አቀረበ።

«ክብርት ዳኛ! ይፈቀድ አይፈቀድ አላውቅም። የወንድሜን ገዳይ አምበርን አቅፌ ይቅርታ እንዳደረግሁላት እንድነግራት እባክዎ ይፍቀዱልኝ!?» ዳኛዋ ያልጠበቁት እና ስሜታቸውን የነካ ጥያቄ ስለነበር እንባቸውን በመሀረባቸው እየጠረጉ ዝም ሲሉት አይን አይናቸውን እያየ አንጀትን በሚበላ ለሆሳስ እንደገና «እባክዎ ...! ? » ሲል ይማፀናቸዋል ። ዳኛዋም በመጨረሻ ይሁንታቸውን ሰጡት። አምበር ከተከሳሽ ሳጥን ተነስታ ቦታም ከምስክሮች ሳጥን ተነስቶ ከዳኛዋ ፣ ከታዳሚው ፣ ከዓለም ካሜራ ፊት ፤ ለአመታት ተነፋፍቀ እንደተገናኘ ፍቅረኛ ተቃቀፉ። በሳግ ስቅስቅ ብለው ተላቀሱ። ይሄን ከስንት አንድ የሚያጋጥም የችሎት ውሎ መደበኛና ማህበራዊ ሚዲያዎች ለመላው ዩናይትድ ስቴትስ አዳረሱት። ነጭ አክራሪ፣ ለዘብተኛ፣ ኢንዲያንስ ፣ ጥቁር ፣ እስፓኒክ ፣ «ብላክ ፓንተር » ፣ ብላክ ላይፍ ማተር ፣ ዴሞክራት ፣ ሪፐብሊካን ፣ ቲ ፓርቲ ፣ ኬ ኬ ኬ ...፤ ሳይለይ። ቦታም በእቅፉ ስር ሆና ስቅስቅ ብላ በጸጸት የምታነባውን የታላቅ ወንድሙን ገዳይ

«እንደ ሰው እወድሻለሁ። ምንም ዓይነት ክፉ ነገር እንዲደርስብሽ አልፈልግም።» ሲል አደመጡት። ዓለም ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ተመለከተው። ችሎቱ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዋይታ ቤት ይመስል በለቅሶ ተሞላ። የወንድማችንን ፣ የእህታችንን ፣ የአባታችንን ፣ የእናታችንን ፣ የምንወዳትን ፣ የምንወደውን ፣ የቅርብ ቤተሰቦቻችንን ገዳይ ለዚያውም ተመጣጣኝ ፍርድ ባልተሰጠበት ችሎትና ሚዲያ ፊት ይቅር ማለት ለዚያውም ገዳይን አቅፎ ማፅናናትን ለአፍታ በምናባችን ስናንሰላስለው ተምኔታዊ ከአእምሮ በላይ ቢሆንም፤ ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርሁት ዳላስ በዋለው በዚህ ታሪካዊ ችሎት ከሰውነት በገዘፈ ተክለ ሰብዕና ወጣቱ ቦታም ጅን ለዓለም ተገልጧል ። ይህ የይቅርታ እጅ የተዘረጋው ገዳይ የታላቅ ወንድሙ መኖሪያ ቤቱ ድረስ ሄዳ ለፈፀመችው ግድያ በ10 አመት እስር ብቻ እንድትቀጣ ከተወሰነባት በኋላ ነው ።

ጂን ይሄን ሲያደርግ ነጭ ስለሆነች ነው ቅጣቱ የቀለለላት በሚል ቅሬታ በችሎቱ አዳራሽ የሚሰማው ጉርምርታም ጋብ አላለም ነበር። ስለዚህ የይቅርባይነት ጥግ የሰማሁት ከCNN ጉምቱ ጋዜጠኛ ክርስቲያን አማንፓር ነው። የችሎቱን ውሎ የሚያሳየውን ተንቀሳቃሽ ምስል ዩቲውብ ላይ ሰውነቴን እየወረረኝ እንባ እየተናነቀኝ ደግሜ ደጋግሜ ተመልክቸዋለሁ። ምነ ይሄ የይቅርባይነት መንፈስ አትላንቲክን በተአምር ቀዝፎ ቀጣናውን አሳብሮ ኢትዮጵያን ባዳረሰ ብዬ ተመኘሁ። ይቅርባይነት ፣ ፍቅር ግዘፍ ነስቶ የሚዳሰስ የሚጨበጥ መሆኑን ነው የተገነዘብሁት።

በሟች፣ በሟች ወንድምና በገዳይ መካከል የተገነባው የቂም፣ የዘር ፣ የቀለም ፣ የመልካዕ አጥር ፈርሶ በዳላሱ ፍርድ ቤት ይቅርታና ፍቅር ሲነግስ ስመለከት በዚያ የተገኘሁ ያህል ነው የተሰማኝ። ሰው የመሆን ምስጢሩ የተገለጠበት ክስተት ከመሆኑ ባሻገር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደ ፈጣሪ ፍጹም ፍቅር የተገለጠበት መለኮታዊ ክስተት ነው። ወጣቱ ጅን ያለበት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ይቅርባይነትና ፍቅር ከፍ ብሏል። ጥላቻ፣ ልዩነትና ዘረኝነት አየሩን ፣ መልክዓውን በተቆጣጠረበት ዓለም ይህን መሰል ይቅርታ ከሰማይ እንደወረደ መና ቢቆጠር ሊያስደንቀን አይገባም።

የሟች ወንድም ቦታም ጅን ገና የ18 አመት ብላቴና እያለ ነው ይቅርባይነትን ኖሮ በተግባር ያሳየን። የልጅ አዋቂ ሆኖ የይቅርባይነትን አይን፣ ልቡና የገለጠልን። ብዙዎቻችን አይደለም በቦታም ዕድሜ በማምሻ ዕድሜያችን እንኳ ደፍረን «ይቅርታ! » ለማለት ይተናነቀናል። በፋና ቴሌቪዥን ከወላጅ እናቱ ጋር ከ20 አመታት በላይ ተኮራርፎ በጥምቀቱ ሰሞን እንደታረቀ ስንሰማ ብዙዎቻችንን አስገርሞን ነበር። ቂምን በቀልንና ጥላቻን እንደተሸከምን የምናልፍ፣ ወደ መቃብር የምንወርድ መኖራችንን ስንረዳ እንፅናናለን። በወላጆቻችን ፣ በእህት ወንድሞቻችን ፣ በትዳር አጋሮቻችን ፣ በልጆቻችን ፣ በቅርብ ዘመዶቻችን ፣ በአብሮ አደጎቻችን ፣ በክፍል ጓደኞቻችን ፣ በመምህራኖቻችን ፣ ወዘተ . እንዳኮረፍን፣ ቂም እንደያዝን ከዚህ ዓለም በሞት እንለያለን ።

ባስሲልም ከራሳችን ጋር ሳይቀር እንደተጣላን እንደተኳረፍን ወደ ማይቀርበት ዓለም እንሄዳለን። ሌሎቻችን ደግሞ ከአምላካችንና ከተፈጥሮ ጋር እንደተጣላን ይቅር ሳንባባል እንሞታለን። ቦታም ጅን ግን ከዚህ አልፎ የሚወደውን የታላቅ ወንድሙን ገዳይ ነው ይቅር ያላት። አንዳንዶቻችን ፌስቡክ ፣ ቲዊተር ፣ ቴሌግራም ፣ ኢኒስታግራም ፣ ዩቲውብ ፣ ወዘተ... ላይ በተሰጠን አስተያየት መልስ ለመስጠት እንቅልፍ የምናጣ ፣ የስድብ ውርጅብኝ የምናወርድ ፣ ይህ አልበቃ ብሎን ጉድኝታችንን የምናቋርጥ unlike የምናደርግ ከፍ ሲልም ጥርቅም አድርገን የምንዘጋ block በማድረግ ቂማችንን የምንወጣ ጉዶች ነን። በጥሞና በሰከነ አእምሮ ቁጭ ብሎ ተነጋግሮ ልዩነትን የመፍታት ልምምድ የለንም። ፈልጎ ፣ ወዶና ፈቅዶ ባላገኘው ማንነት ሳይቀር የምንጣላ፣ ቂም የምንይዝ እና ለበቀል የምንነሳ ስንት ደመ ነፍሳውያን አለን። በቀደሙ ነገሥታት የተፈፀመን ስህተት በዚህ ትውልድ ለማወራረድ የምንንቀዠቀዥ ከንቱዎች ነን ።

ጂን «ይፈቀድ አይፈቀድ እርግጠኛ አይደለሁም። የወንድሜን ገዳይ አቅፌ ይቅር እንድላት የተከበሩ ዳኛ ሊፈቅዱልኝ ይችላሉ !? እባክዎ ! » የሚለው ድምፅ ዛሬ ድረስ በእዝነ ህሊናዬ ይሰማኛል። የዕለቱ ዳኛ ታሚ ኬምፕ ባልጠበቁት ጥያቄ ግራ ተጋብተው ይሁን በጅን የይቅርባይነት ልብ ልባቸው ተነክቶ ለደቂቃዎች ዝምታን ከመረጡ በኋላ ሲፈቅዱለት የሚያሳየውን ምስልም በመደነቅ ከመድገም በላይ ሰላልሸዋለሁ። የወንድሙ ገዳይ የዳላስ ፖሊስ ባልደረባ የነበረችው ነጯ አምበር ጉይገርም 911 ላይ ደውላ ከተናገረችው እንደተደመጠው፤ « ሥራ ውዬ ቤቴ እንደደረስሁ በሩ ተከፍቶ ጠበቀኝ። እኔም ሌባ የገባ ስለመሰለኝ ሽጉጤን አቀባብዬ ወደ ሳሎን ስዘልቅ እንግዳ ሰው ሶፋ ላይ ተቀምጦ ሳይ ደንግጬ ተኩሼ ገደልሁት። ወደ አእምሮዬ ስመለስ ግን ለካ የገባሁት እኔ ቤት ሳይሆን በስህተት ሟች ቤት ነበር። «የገዳይን ሰንካላ ቃል አምኖ ለመቀበል አዳጋች ቢሆንም በዚህ መንገድ የወንድሙን ሕይወት ለነጠቀች ፖሊስ ነው ጅን ይቅርታ ያደረገላት። ሌሎች የቤተሰቡ አባላትና የጥቁር መብት ተሟጋቾች ግን ገዳይ በ10 አመት እስር ብቻ መታለፏን በመቃወም ከፍርድ ቤቱ ፊት ለፊት ቁጣቸውን በመፈክር እየገለጹ ነበር። አንተ ፣ አንቺ ብትሆን /ኚ / ታደርገዋለህ / ጊዋለሽ !?

## እንደ መውጫ

የእርቅ፣ የይቅርታ፣ የፍቅር ተምሳሌት፣ አባት ፣ ረቡኒ/አስተማሪ / የሆነው የደቡብ አፍሪካ የፀረ አፓርታይድ ትግል መሪና የነፃዋ ደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው ጥቁር ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላ /ማዲባ / እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1995 ለንባብ በበቃው " Long Walk to Freedom" በተሰኘው ድንቅ ግለ ታሪክ መፅሐፉ ፤ " ሁሉም ሰው ጥላቻን ተምሮ እንጂ ከእናቱ ማህፀን ይዞት አልተወለደም። ጥላቻን የተማረ አእምሮ ደግሞ ፍቅርንና እርቅን መማር አይከብደውም። " እንዳለው ጅን ፍቅርን ይቅርታን ከእናቱ ማህፀን ይዞት አልተወለደም። ከፈጣሪው ከእምነቱ ተምሮት እንጂ ። እኛም ከጅን የይቅርታ ልብ ብዙ ብዙ መማር ማትረፍ እንችላለን። ጥላቻን ልዩነትን ባለፉት 50 አመታት ተቋማዊና መዋቅራዊ ሊባል በሚችል ደረጃ ተጋትነው እንጂ ከእናታችን ማህፀን ይዘነው አልተወለድንም። ከእናታችን ማህፀን ይዘነው ያልተወለድነውን ግን በአንድም ሆነ በሌላ መልክ የተማርነውን ጥላቻ ፣ ልዩነትና ቂም በቀል ፤ ከአእምሮአችን ለመሰረዝ ፣ ለማጥፋት እንደ ጅን ካሉ ባለግዙፍ ተክለ ሰብዕና ባለጸጋዎች መማር እንችላለን። ከእነ ማንዴላ ፣ ማህተመ ፣ ሉተር ተዝቆ የማያልቅ የይቅርታ መዝገብም መማር ይቻላል።

ለዚያውም ጥላቻን ከመማር ይልቅ ፍቅርንና ይቅርባይነትን መማር ይቀላል። ምክንያቱም ፍቅር ይቅር ባይነት አምላካዊ ሲሆን ጥላቻ ደግሞ ሰይጣናዊ ነው። የሰው ልጅ ደግሞ አምላኩ በአምሳሉ የፈጠረው ስለሆነ አእምሮው ለፍቅር ፣ ለይቅርታ ይቀርባል ። ያደላል ። ከጅን ይቅርባይነትን ያረጋገጥነው ይሄንኑ ነው። መቼም ስለ ፍቅር፣ ይቅርባይነት በተነሳ ቁጥር ከፈጣሪ ቀጥሎ ስሙ የሚወሳው ማንዴላ ነው። ከፍ ብዬ በጠቀስሁት መፅሐፉ ስለ ይቅርባይነት ከፍታና ኃያልነት ፤ «ይቅርባይነት ነፍስን አርነት ያወጣል። ፍርሀትን ያስወግዳል። » ሲል እማኝነቱን ፣ ምስክርነቱን ገልጿል። ስለዚህ ይቅር በመባባል ነፍሳችንን ከባርነት ነፃ እናውጣ። በይቅርባይነት ቀይዶ አላላውስ ካለን የፍርሀት ቆፈን እንላቀቅ ።

ወገኖቼ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደልኋችሁ፤ በዚህ ጋዜጣ በምጽፋቸው መጣጥፎች የተቀየማችሁ ብትኖሩ ከእግራችሁ ስር ወድቄ ይቅር እንድትሉኝ እለምናለሁ። እንዲሁም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደላችሁኝንም ከልብ ይቅር ብያለሁ ።

አገራዊ ምክክር፣ ሰላምና እርቅ ለመላው ኢትዮጵያውያን !

አሜን።

**በሟች፣ በሟች ወንድምና በገዳይ መካከል የተገነባው የቂም፣ የዘር ፣ የቀለም ፣ የመልካዕ አጥር ፈርሶ በዳላሱ ፍርድ ቤት ይቅርታና ፍቅር ሲነግስ ስመለከት በዚያ የተገኘሁ ያህል ነው የተሰማኝ**

ማህበራዊ

ሀገርኛ

# ከአሻራ አኗሪነት ወደ አሻራ አሻጋሪነት የተሻዘው ማንነት

ጽጌረዳ ጫንያለው

እኛ መልከ ብዙ፣ ልምደ ብዙ አገር ነን።ታሪክና ብዙ ተሞክሮችን የቀመርንና ለሌላ የምናካፍልም እንደሆንን ብዙዎች ይመሰክሩልናል።ለዚህም አንዱ ማሳያ ተፈጥሮ ካሳመረልን ውጪ በራሳችን አረንጓዴ ምድር ለመፍጠር የምናደርገው ጥረት ነው።የአየር ንብረት ለውጥ የሚያመጣውን ችግር ለመመከትም ከሌሎች አገራት በይበልጥ የምንተጋ ሕዝቦች ነን።ይህ አገርኛ ልማዳችን መቼ ጀመረ? ከተባለ የተለያዩ ጥናታዊና ታሪካዊ ጽሑፎች እንደሚያመላክቱት በ14ኛው ክፍለ ዘመን በንጉሥ ዘረ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ነው።ለረጅም ዓመታት በዘመቻ ችግኝ ተተክሏል፤ እንክብካቤም ተደርጎለታል።ይህ የሆነውም በራሱ በሕዝቡ አማካኝነት እንደነበር ከአረንጓዴ ልማት ጋር በተመለከተ ብዙ ጥናትና ምርምሮችን ያደረጉት ዶክተር ተወልደ ብርሃን ገብረእግዚአብሔር ይናገራሉ።

ኢትዮጵያውያን የአካባቢ እንክብካቤን የሚያደርጉት ለዘመናዊው ትውልድ ጭምር የሚያስተላልፉት ልምድ እንዲኖር በማሰብ ነው የሚሉት ዶክተር ተወልደብርሃን፤ መሬቱ እንዳይሸረሸር እርከኖችን ይሠራሉ፤ ዛፎችን ተክለውም ይንከባከባሉ።በዚህም ባሕልና ተፈጥሮን ማጣመር የሚችሉ ሕዝቦች ናቸው።በራሳቸው ተነሳሽነትም ምድሪቱን አለምልመዋታል።መጀመሪያ ከታች ወደላይ በማምጣት ከዚያ ደግሞ ከላይ ወደታች በማውረድ ተግባሩን የከወኑ ድንቅ ሕዝቦች መሆናቸውንም ያነሳሉ።

« Status, Challenge and Opportunities of environmental Management in Ethiopia» በሚል በታተመ ጆርናል ላይ በንጉሥ ዘረ ያዕቆብ ዘመን በዘመቻ ከተተከሉና ተጠብቀው ከቆዩ ደኖች ወፍ ዋሻ፣ ጅባት፣ መናገሻ እና የየረር ተራሮች ጥብቅ ደኖች ይጠቀሳሉ።በመንግሥት ደረጃ ችግኞችን አፍልቶ መትከል የተጀመረው ግን በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን እንደነበር ይነሳል የሚሉት ተመራማሪው፤ ይህም በ16ኛው ክፍለ ዘመን አጼ ልብነ ድንግል ከወፍ ዋሻ ዘርና ችግኞችን ወስደው ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ በሚገኝ መናገሻ ሱባ የሚባል ሥፍራ የሃበሻ ጽድ የተከሉበት ነው።በመቀጠል አፄ ምኒልክ ባህርዛፍን ከአውስትራሊያ በማስመጣት ተክለዋል። በአገሪቱ ያለውን የማገዶና የቤት መሥሪያ ቁሳቁስ እጥረት ለመቀነስም የባህር ዛፍ ተክልን ከአውስትራሊያ አስመጥተው በመትከልና በማስተከል አፄ ምኒልክ «ዘመናዊ» እፅዋትን ለኢትዮጵያ አስተዋውቀዋል።በወቅቱ የደን መጨፍጨፍን ለመከላከል «ሁሉም በግለሰብ መሬት ላይ ያሉ ዛፎች የመንግሥት ንብረት ናቸው» ሲሉ አውጀው እንደነበር በዚሁ ጆርናል ላይ መጠቀሱን ያብራራሉ።

ደኖች የሕዝብ ሀብት እንደሆኑ በኅብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ እንደነበር ይነገረናል።ከዚያም በኋላም ቢሆን ኢትዮጵያን ያስተዳደሩ መሪዎች የተለያዩ ስልቶችን እየተጠቀሙ ችግኞችን በዘመቻ ተክለዋል።ለዚህም ምስክር የሚሆኑት በቤተክርስቲያንና መስጊዶች እንደነበሩም ይናገራሉ።

በዘመነ ነገሥታት በተለያዩ ምክንያቶች ነገስታቱ መናገሻቸውን ይለዋውጡ እንደነበር ይታወቃል።ለዚህ ማሳያው ደግሞ አፄ ምኒልክ ሲሆኑ፤ መኖሪያቸውን ሲለዋውጡ አብረው ችግኝ መትከልን እንደዋና ተግባራቸው አድርገው ይጓዙ ነበር።በፍጥነት ማደግ የሚችልና ራሱን በፍጥነት የሚተካውን ባህርዛፍን በአማካሪያቸው አማካኝነት የመረጡትም ለዚህ እንደነበር ታሪክ ይነገራል።

ከምኒልክ ቀጥሎ አፄ ኃይለሥላሴም ቢሆን ችግኝን ለመትከልና ለመንከባከብ ብዙ የለፉ ናቸው።የደን አዋጅን በማውጣት በርካታ ሥራዎች ከውነዋል።ለአብነት «አጼ ኃይለሥላሴ ችግኝ መትከልን እንደ አንድ የመንግሥት ሥራ አድርገው ወስደውት እንደነበር ይወሳል።በተጨማሪ እርሳቸው ደን መጠበቅና ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ፓርኮች እንዲቋቋሙ ምክንያትም ነበሩ።ለዚህም ማሳያው አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ነው።

ወደ ደርግ ዘመነ መንግሥት ስንገባም ይህ ኢትዮጵያዊ ባህል የአካባቢ ጥበቃን የተመለከቱ ፖሊሲዎች ጭምር ተቀርፀውበት የቀጠለ ነው። ዋነኛ ትኩረታቸው ግን የዱር እንስሳት ጥበቃ ላይ እንደነበር ጥናቶች ያሳያሉ። በተለይ በጎርጎሮሳውያኑ አቆጣጠር






1973/74 (1966 ዓ.ም) በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የተከሰተው ርሃብና ድርቅ፤ አካባቢ ጥበቃ ላይ ጠንክሮ ለመሥራት እንዳነሳሳ ይጠቀሳል። በአጠቃላይ ደን ሥራ ላይ ከፍተኛና የተቀናጀ ሥራ ለመሥራት ዝግጅት ተደርጎ፣ ቦታዎች ተመርጠው፣ ችግኞች ተፈልተው፣ ለማኅበረሰቡ አነስተኛ ድጎማ በማድረግ፤ በተራቆቱ ቦታዎች ችግኞች እንዲተከሉ መደረጉም ይወሳል።

ኢህአዴግ ላይ ስንገባ ደግሞ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ማንሳት ግድ ይለናል።በተለይ ዋናው የትኩረት አቅጣጫ የአየር ንብረት ለውጥ እንደነበር ይታወሳል።ችግኝ መትከልና አካባቢን መንከባከብ እንደ አንድ ትልቅ ሥራ ተደርጎ ይወሰድ ነበር።ይህ ወቅት የልማትና የአካባቢ ጥበቃ ተቋማት የተመሠረቱበትም ነው። በፖሊሲ ደረጃም ሥነ ምህዳርን፣ አካባቢን፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን በሚመለከት ግብ ተቀምጦለት እንቅስቃሴ ተጀምሮበት ነበር፡፡

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን እየመሩ ያሉት ዶክተር ዐቢይ አሕመድም 'አረንጓዴ አሻራ' በሚል የተደረገው አገር አቀፍ የችግኝ መትከል ዘመቻ ይህንኑ የሚያጠናክር እንደሆነ ማንም አይክደውም።ዘመቻው በፍላጎት ላይ የተመሠረተ እና በስፋት በርካታ ችግኞች የተተከሉበት መሆኑ ደግሞ ልዩ ያደርገዋል።ይሁን እንጂ እንደቀደመው ጊዜ ባህል አድርጎ ማኅበረሰቡ ችግኞችን መትከል ይገባዋል።ምክንያቱም አሁን ላይ ከከተሞች መስፋፋትና ሥልጣኔ ጋር ተያይዞ ዓለም በአየር ንብረት ለውጥ ችግር እየታመሰች ነው።ኢትዮጵያም ብትሆን የገፈቱ ቀማሽ እየሆነች መጥታለች።ለዚህ ደግሞ መፍትሄው አንድናአንድ ሲሆን እርሱም ችግኝን መትከል ነው።እናም ቀስቃሽ ሳንሻ ይህንን ማድረግ የውዴታ ግዴታችን ሊሆን ይገባል።

ማኅበረሰቡን ማነሳሳትና ወደ ቀደመው ባህሉ ማሻገር አስፈላጊ ነው።አገርኛ ባህላችን ደግሞ እንዲጎለብት ከዚህ አማራጭ ውጪ ሌላ ሊመጣ የሚችል ነገር አይኖርም።ስለሆነም ሪከርድ በተያዘበት ጊዜ በአንድ ጀንበር የተተከሉት ከ350 ሚሊዮን በላይ ችግኞች እንደነበሩን ሁሉ አራት ቢሊዮን ችግኝን ተክለን አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት ሊሸፍን የሚችል የአገር ሀብት ማምረት እንደምንችል በማመን ወደ ተግባሩ መግባት ይጠበቅብናል።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት በአንድ ወቅት ባወጣው ዘገባ እንዳስቀመጠው፤ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነስ በመምጣት አሁን ላይ ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት 15 በመቶ ወይም 17 ሚሊዮን ሄክታር ብቻ መሸፈኑን በቅርቡ የወጣው "Mass tree planting Prospects for a green legacy in Ethiopia" የተሰኘ ሪፖርት ያሳያል።ከዚህ ውስጥ ደግሞ 15 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታሩ የተፈጥሮ ደን ነው።የተቀረው በችግኝ ተከላ የተሸፈ እንደሆነም ጥናቱ አመላክቷል።በተጨማሪም አገሪቱን በደን ምንጠራ ባዶ የሆነና ደንን መልሶ ለማልማት ምቹ የሆነ 18 ሚሊዮን ሄክታር ባዶ መሬት እንዳላት ሪፖርቱ ያሳያል።እናም ችግኙ ፀድቆ ደን መሆን ሲችል የኢትዮጵያ የደን ሽፋን በአንድ በመቶ ሊያድግ እንደሚችል ይገመታልና ያንን ማድረጉ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ድርሻ ይሆናል።

ኢትዮጵያ በአቶ መለስ ዜናዊ ይፋ በተደረገው «ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ» ስትራቴጂን ቀርፃ መንቀሳቀስ ላይ መሆኗ ሲታወቅ የበርካታ አገሮችን ቀልብ ስባ ነበር።በተለይም ከበለፀጉ አገሮች መካከል ኖርዌይ፣ እንግሊዝ፣ ዴንማርክ፣ ስዊድን፣ ፈረንሳይና አሜሪካ የመሳሰሉ አገሮች ኢትዮጵያ እየተገበረችው ላለው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ድጋፋቸውን ከሰጡ መካከል ይገኛሉ።ስለዚህም ከአገራዊ ልምዷ ባሻገር የምትነድፋቸው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂዎች ጭምር ሌሎችን የሚያስቀና እንደነበር መረዳት ይቻላል።

ኢትዮጵያ በአገር ውስጥ የምታከናውናቸው ሥራዎች የራሷን ልማትና ዕድገት የሚያፋጥኑ፣ ለዓለም ሥጋት የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከልና አደጋዎቹን ለመቀነስ ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚኖረውም በእጅጉ ታምኖበታል።ለአየር ንብረት ለውጥ መባባስ ትልቅ ሚና የነበራቸው አገሮች ሳይቀሩ እንኳን አገራችን ለምታከናውነው የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂ ድጋፋቸውን ለመስጠት የወሰኑት ችግሩ ያስተሳሰራቸውና የጋራ ጥቅም ወደሚያስገኝ መፍትሔ የሚወስዳቸው ሆኖ በማግኘታቸው መሆኑን መገመት አይከብድም።

ኢትዮጵያ የያዘችው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋምና ዝቅተኛ የካርበን ልቀት መጠን እንዲኖር የሚያደርግ አብዮት ነው።ስትራቴጂው በአንድ ጎን ልማትና ዕድገቷን የሚያፋጥንና ዘላቂነቱን አስተማማኝ የሚያደርግ አካባቢ እንደሚፈጥር ጥናቶች ይጠቁማሉ።ተፈጥሮን ከመንከባከብና ተጠቃሚ ከመሆን በተጨማሪ ለብክለትና ለውድመት ከሚዳርጉ አደጋዎች ጠብቆ ለማቆየትም ሁነኛ መፍትሔ ያዘለ ሆኗል።

በ2017 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ. በ2025) መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ ራዕይ ሰንቃ በመንቀሳቀስ ላይ የምትገኘውን ኢትዮጵያ፣ በተለይ አረንጓዴ ልማት ለሕዝቧ የሕልውና እና የኑሮ መሠረት በመሆኑ፣ እየተሠራ ያለው ሥራ ዓለም ጭምር በሞዴልነት እየወሰደና እየሠራበት እንደሚገኝ የዘርፉ ምሁራንና ጥናቶች እያረጋገጡ ያሉት።

የአገራችን የደን ሀብት ታሪክ በጣም ወደኋላ ብንሔድ የምድሪቱ 120 ሚሊዮን ሄክታር 60 በመቶ በሚሆን ደን ተሸፍኖ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይጠቁማሉ።ቀደም ባለው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከ1375 እስከ 1404 አገሪቱን ያስተዳደሩት አፄ ዳዊት የደን እንስሳትንና ገደብ የለሽ የአደን ጨዋታን ለመከላከል አገሪቱን ለሰባት የአካባቢ ጥበቃ ጣቢያዎች ጠባቂ ሰው በመመደብ ከፋፍለውት እንደነበር ዜና መዋዕላቸው ይነግረናል።በተመሳሳይም ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብም የጅባትን ደንና የወፍ ዋሻን ውኃ-በል (watershed) የደን ክምችት እንዲጀመር አድርገው ነበር።የወጨጫንና የየረር ጋራዎችን በደን በማልማት እንዲሁም «የንጉሥ የደን ክልል» በማድረግ አገሪቱን በደን የማልበስ ተግባር በስፋት እንደፈጸሙ ታሪካቸው በስፋት ያወሳል፡፡

የደን ሀብትን ጠቃሚነትን በእጅጉ የተገነዘቡት ዐፄ ምኒልክም፤ «የንጉሥ የደን ክልል» የሚለውን እሳቤ አጽንዖት በመስጠትም በዘመናቸው የመጀመሪያውን የደን ሥርዓት መሥርተው ነበር።ዐጤ ምኒልክ የመጀመሪያውን የደን ሕግ ለማርቀቅም የውጭ አገር ባለሙያዎችን ቀጥረው እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ።ይህም ሕግ ደን ሁሉ የመንግሥት ንብረት እንዲሆን ይደነግጋል።

አገሪቱን በደን ለማልማት ካላቸው ቅንአት የተነሣም በፍጥነት የሚያድጉ ዛፎችን ከሌሎች አገር ያስመጡ ነበር።ንጉሡ የደን አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ለማቋቋም ካላቸው ፍላጎት የተነሣ የውጭ አገር ዜጋም ቀጥረው ነበር።ከዚህ በተጨማሪም ሕዝብ የተፈጥሮ የደን ሀብትን እንዲንከባከብ ያበረታቱ ነበር።ንጉሡ የደን አጠባበቅን በተመለከተ ያወጡት ሕግ ደንን አላግባብ የሚጨፈጭፉ ሰዎችን ንብረታቸውን በመውረስና እስከ ሞትም በሚያደርስ የቅጣት ርምጃ የጠነከረም ነበር፡፡

'የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ' በማስቀጠል ረገድም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በስፋት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ።እንደ አብነትም ዶክተር ዐቢይ በመዲናችን በአዲስ አበባ ያስጀመሯቸው ታላላቅ ፕሮጀክቶች አረንጓዴ ኢኮኖሚን፣ የአካባቢ ጥበቃንና የተፈጥሮ ሀብት መንከባከብን ትኩረት ያደረገ መሆኑን ልብ ይሏል።የተፈጥሮ ሀብትም ሆነ የዕፅዋቶችና የደኖች መመናመን ጉዳይ በኢትዮጵያ ላይ እያደረሰ ያለው ጥፋትና ቀውስ ከፍተኛ መሆኑ ከግምት ውስጥ ያስገቡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ መላው የአገራቸውን ሕዝብ ከጎናቸው በማሰለፍ የአረንጓዴ ልማት ዐርበኛ በማድረግ ረገድ ትልቅ ስኬትን እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡

ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ ከምሁር እስከ አፈ ነቢብ... ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ያሳተፈው የችግኝ ተከላ ዘንድሮም በስፋት ቀጥሏል።ኢትዮጵያን በአፍሪካና በዓለም አቀፍ መድረክ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ/ልማት ሞዴል አድርጓታልም።የደን ሀብቶቻችን ሊያበረክቱ የሚችሉትን እምቅ ጠቀሜታዎችም ግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ለራሱ፣ ለልጆቹና ለመጪው ትውልድ ሲል በዚህ የአረንጓዴ ዘመቻ ላይ በስፋት እንዲሳተፍ በተደጋጋሚ ላስተላለፉት አገራዊ ጥሪ ከሁሉም የማኅበረሰሰብ ዘንድ ተግባራዊ የሆነ ምላሽን እየተቸረው ነው፡፡

አገራችን ካሏት እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶችና የመልሚያ ዕድሎች አንዱ የደን ሀብት ሲሆን፤ የደን ሀብቶቻችንን መጠበቅ፣ ማልማት እና በዕቅድ ጥቅም ላይ ማዋል ኢኮኖሚያዊ፣ ሥርዓተ-ምሕዳራዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ጥናቶች ያመላክታሉ።ጃሬድ ዳይመንድ (Collapse – ውድቀት በተሰኘ መጽሐፉ) «የተፈጥሮ ሀብቶቻቸውን በተገቢው መንገድ የማይዙ እና ጥቅም ላይ የማያውሉ ማኅበረሰቦች ላልታሰበ ሥርዐተ-ምሕዳራዊ አጥፍቶ የመጥፋት አደጋ ይጋለጣሉ፤» ይላል።

የደኖች መመናመን፣ የዕፅዋት ዓይነት እና ብዛት መቀነስ፣ የደን ለበስ መሬቶች መራቆት፣ ሚዛን ያልጠበቀ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለተጠቀሰው አደጋ ምክንያት መሆናቸውን ከምድረ ገጽ የጠፉ ማኅበረሰቦች ታሪክ ያስረዳል።ስለሆነም ከዚህ አደጋ ለመትረፍ ዛፍ መትከል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሊሆን ይገባዋል፡፡

የብዝሀ ሕይወት ሀብትና ሥርዓተ ምሕዳር በፕላኔታችን የሰው ልጅን ጨምሮ ለሌሎች ሕይወት ላላቸው ነገሮች አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም።ከዚያም ባሻገር የተለያዩ አስቸጋሪ የበሽታ ወረርሽኞችን ከመከላከልና በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የሚደርሱ ጉዳቶችን በመቀነስ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው።እናም ኢትዮጵያውያን አረንጓዴ ውበትና አረንጓዴ ሕይወት ይኖራቸው ዘንድ ችግኝ መትከል፣ ዕፅዋቶችን መንከባከብ፣ ደኖቻችንን ከጭፍጨፋ መከላከል የሁሉም ሰው ኃላፊነት ነው።በዚህ ክረምትም ሁሉም ሰው ችግኝ በመትከልና የተተከሉትንም በመንከባከብ የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል።ይህ ጊዜ አገር በቀሉን ልምዳችንን በመጠቀም እኛም ከችግራችን የምናላቀቅበት ነውና ችግኞችን በመትከል ታሪካዊ አረንጓዴ አሻራችንን ለራሳችን፣ ለአገራችን፣ ለትውልድ ማሳረፊያ እናውለው በማለት ለዛሬ የያዝነውን ሀሳብ ቋጨን።ሰላም!!

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ወጣቶች በሥነ-ጥበብ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት


ወጣት ልዑልሥሳሴ ፀጉ፤


አቶ ንጉሴ አድነው


ወጣት ካሊድ ታረቀኝ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ወጣት ካሊድ ታረቀኝ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ከተማ ክፍለከተማ ወረዳ አራት ነዋሪ ነው። የሰከላ ፊልም ፕሮዳክሽን ማኔጀርም ሲሆን የዛሬ አመት እርሱ በሚኖርበት ወረዳ በተዘጋጀ የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት የቪዲዮና ካሜራ ስልጠና አግኝቷል። በኋላም ደግሞ ይህንኑ የቪዲዮና ካሜራ ትምህርት ከግራፊክ ዲዛይን ጋር አጣምሮ በግሉ ተምሯል።

በዘንድሮው የክረምት ወቅት ደግሞ እርሱም በተራው ከዚሁ የቪዲዮና ካሜራ ጥበብ ጋር በተያያዘ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከሚሰጡ ወጣቶች ውስጥ አንዱ ለመሆን በቅቷል። በዚህ የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃ ግብር በቪዲዮ ኤዲቲንግና ካሜራ ሞያ ወጣቶችን ለማሰልጠንም ወጣቶችን እየመዘገበ ይገኛል።

እስካሁንም ከዘጠና በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችን መዝግቦ ከመጪው ሐምሌ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ስልጠናውን ለመስጠት ዝግጅቱን አጠናቋል። በሂደት ደግሞ ከቪዲዮ ኤዲቲንግና የካሜራ ሞያ ስልጠና በተጨማሪ ለወጣቶች የቋንቋ ስልጠናዎችን ለመስጠት እቅድ ይዟል።

‹‹ለእኔ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ካለኝ ነገር ላይ ጥቂቱን ለሌሎች ማካፈል ነው›› የሚለው ወጣት ካሊድ፤ ያለኝን የቪዲዮ፣ ካሜራና የግራፊክ ዲዛይን ሞያ ለወጣቶች በነፃ ሳካፍል ትልቅ ክብር ይሰማኛል ሲል ይናገራል። ይህን በማድረጌ ከገንዘብ በላይ ትልቅ የአእምሮ ርካታም ይሰማኛል ይላል። በተለይ ደግሞ ይህን ሞያውን የሚያካፍለው እዚያው ራሱ የኖረበት አካባቢ ላሉ ወጣቶች በመሆኑ ራሱ ተምሮ መልሶ የአካባቢውን ወጣት እያገለገለ በመሆኑ ደስታው ወደር እንደሌለው ይገልፃል።

በተመሳሳይ በሌሎች ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ሥራዎችን እየሠሩ ያሉ ወጣቶች ከሚያገኙት ትርፍ በዘለለ ባላቸው ሞያ በበጎ ፍቃደኝነት ሌሎችን ማስተማር፣ ማገዝና መርዳት እንዳለባቸውም ይመክራል።

ወጣት ልዑለሥላሴ ፀጉም በተመሳሳይ የዚሁ ወረዳ ነዋሪ ሲሆን የኬዛ አፍሪካ ፕሮዳክሽን ምክትል ሥራ አስኪያጅ ነው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ2009 ዓ.ም የፍልስፍና ትምህርት ምሩቅም ነው። ከዚሁ ጎን ለጎንም በፊልም ሥራ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ራሱን አስተምሯል። ከምርቃት በኋላ ደግሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት በመግባት የፊልም ሥራ ተምሯል።

እርሱ እንደሚለው ኬዛ አፍሪካ በዋልታ ኤፍ ኤም 105 ነጥብ 3 ላይ የሬዲዮ ፕሮዳክሽን ይሠራል። አፍሪካዊነትንና ፓን አፍሪካኒዝምን በፊልሞች፣ በተለያዩ የሥነጽሑፍ ዝግጅቶችና በፓናል ውይይቶች ለሕዝቡ ለማስተዋወቅ ደግሞ የኬዝ አፍሪካ ፕሮዳክሽን ዋነኛ አላማ ነው። በተለያዩ ዘርፎችና መንገዶች ውብ አፍሪካን ለመፍጠርና አፍሪካ ተፅእኖ ፈጣሪ እንድትሆን እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል። በወረዳውም ቤተ መጽሐፍት ለመክፈት እቅድ ይዟል።

በወረዳው የዘንድሮው የክረምት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሀግብር ከሚሳተፉት ውስጥም አንዱ ኬዛ አፍሪካ ሲሆን በፊልም ሥራ፣ በትወና፣ ዳይሬክቲንግ፣ ኤዲቲንግ ስክሪፕት ራይቲንግ ወጣቶችን ለማሰልጠን ምዝገባ ጀምሯል። እስካሁንም ዘጠና የሚሆኑ ተማሪዎች ይህን ስልጠና ለመከታተል ተመዝግበዋል።

ከዚህ ባለፈ በሥነጽሑፍ ሊትሬቸርና በቋንቋ / እንግሊዝኛ፣ ስዋሂሽ፣ ፈረንሳይኛና አረብኛ ቋንቋ/ ከወረዳው ጋር በመነጋገር ወጣቶችን ለማስተማር አቅዷል። እስከ ሐምሌ 2 ቀን 2014 ዓ.ም ለወጣቶቹ ገለጻ ለመስጠት ታስቧል።

‹‹ባለኝ ሞያ ሌላውን ሰው መጥቀም መቻሌ ትልቅ ደስታ ይሰጠኛል›› የሚለው ወጣት ልዑለሥላሴ በግሌ እንኳን ስኬት ባመጣ በአገር ደረጃ ውጤት የማያመጣ በመሆኑ ይህን ለውጥ ለማምጣት ሁሉም ወጣት ከሌላው ጋር ተባብሮ ሊሠራ እንደሚገባ ይጠቁማል። ለወጣቶች በሞያው እያበረከተ ያለውን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለአገር እንደሚያበረክተው አስተዋፅኦ አድርጎ እንደሚቆጥረውም ይናገራል።

ራስን ለመደጎም ለትርፍ መሥራት አስፈላጊ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ወጣቶች ከሥራ ውጪ ያላቸውን ጊዜ፣ እውቀት፣ ገንዘብ ሌላም ነገር በበጎ ፍቃደኝነት ለሌሎች ወጣቶች ቢያበረክቱ በሥራቸው ከሚያገኙት ትርፍ በዘለለ የአእምሮ እርካታም እንደሚያገኙ ወጣት ልዑለሥላሴ ይገልፃል። ከዚህ አንፃር ወጣቶች ባላቸው ትርፍ ጊዜ በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ላይ መሳተፍ ማኅበረሰቡን መጥቀም እንዳለባቸው መልዕክቱን ያስተላልፋል።

በተለይ ደግሞ ወጣቶች ያላቸው ትርፍ ሰዓት በሻይ ቡና እንደሚቃጠልና ሆኖም ይህ ጊዜ ለሌሎች ትልቅ ዋጋ እንዳለው በማሰብ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ ቢያውሉት ራሳቸውም ረክተው ሌላውም ተጠቃሚ የሚሆንበት ዕድል ያለ በመሆኑ ትርፍ ጊዜያቸውን በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ እንዲያውሉት ይመክራል።

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት አስተዳደር ኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ንጉሴ አድነው እንደሚሉት የክረምት የወጣቶች በጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃግብር በየአመቱ ይካሄዳል። የዘንድሮው መርሃግብር ግን ቀደም ብሎ የተጀመረ በመሆኑ ከበፊቱ ለየት ያደርገዋል።

በዚህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃ ግብርም ወደ ዘጠኝ የሚደርሱ ወሳኝ ተግባራት አሉ። እነዚህ ዘጠኝ ተግባራት ደግሞ አሥራ አራት የሚጠጉ ዝርዝር የበጎ ፍቃድ ተግባራትን አቅፈዋል። 567 የሚሆኑ ወጣቶችም በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዘርፎች እየተሳተፉ ይገኛሉ። ወጣቶቹ ከሚሳተፉባቸው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዘርፎች ውስጥም የቤት እድሳት፣ ትራፊክ ማስተባበር፣ ደም ልገሳ፣ ችግኝ ተከላና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ኃላፊው እንደሚሉት በበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃ ግብሩ የሚሳተፉት ወጣቶች በወረዳው በኩል በተሠሩ የማስታወቂያና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ነው። ወጣቶች በብዛት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ላይ በማናገር፣ ስልጠና በመስጠትና ድጋፍና ክትትል በማድረግ በዚህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሃ ግብር እንዲሳተፉም ተደርጓል። የተለያዩ ወጣት እድሮችና ማህበራትን በመጠቀምም ወጣቶቹ ወደዚህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንዲታቀፉ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ከአምናው ጋር ሲነፃፀርም የዘንድሮው የክረምት ወጣቶች በጎ ፍቃድ አገልግሎት መሻሻል ያሳየና በቁጥርም በዓይነትም ከፍ ያለ ነው። አምና 300 አካባቢ የነበረው የወጣት በጎ ፍቃደኞች ቁጥርም ዘንድሮ ወደ 567 ከፍ ብሏል። በየጊዜው ወጣቶችን ሊስቡ የሚችሉ ተግባራት በወረዳው በኩል መከናወናቸው ደግሞ ለቁጥሩ መሻሻል አስተዋፅኦ አድርጓል።

ለአብነትም አምና የቪዲዮና ፎቶግራፍ ኤዲቲንግ ትምህርቶች በመጀመራቸው በዚህ ዘርፍ ሌሎች ወጣቶችን የሚያስተምሩ በጎ ፍቃድ ወጣቶች ቁጥር ከፍ ብሏል። ትምህርቱን ተምረው ዳግም በጎ ፍቃደኛ የሆኑ ወጣቶችም ተፈጥረዋል። በዘንድሮው የክረምት ወቅት ደግሞ አገልግሎቱን ሰፋ በማድረግና የተለያዩ ማበረታቻዎችን ለምሳሌ እውቅናና ሽልማት በመስጠት በአጠቃላይ የፊልም ሥራና የሥነ ጽሑፍ ትምህርቶች እንዲሁም በዲሽ ጥገና ትምህርት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ወጣቶች ቁጥር እንዲጨምር ተደርጓል።

በዚህ የክረምት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ወጣቶች ከሚሳተፉባቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ የቤት እድሳት ሲሆን እንደ ወረዳ አራት 29 የሚሆኑ ቤቶችን ለማደስ እቅድ ተይዞ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በደም ልገሳም ከ500 ዩኒት በላይ ደም ለማሰባሰብ ታቅዶ እየተሠራ ነው። በአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብርም 25 ሺ ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ተከላው ተጀምሯል።

በተመሳሳይ በፅዳት ዘርፍም የተደፈኑ ቦዮችንና አካባቢን የማፅዳት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።ከ60 በላይ ወጣቶች የሚሳተፉበት የትራፊክ አገልግሎትም በወረዳው በሚገኙ ሦስት አደባባዮች ላይ በፈረቃ እየተካሄደ ነው። ከዚሁ ጎን ለጎንም በትራፊክ ደህንነት ዙሪያ በነዚሁ ወጣቶች አማካኝነት የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ይሰጣሉ።

ከጤና ጋር በተያያዘም በተለይ በኤች አይ ቪ ኤድስ ዙሪያና ሌሎች ተዛማች በሽታዎች ላይ በጎ ፍቃድ ወጣቶቹ ለኅብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን እየሰጡ ይገኛሉ።

አሁን ባለው ሁኔታም የዘንድሮው የክረምት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል። 29 ቤቶችን ለማደስ እቅድ ተይዞም ከእቅድ በላይ 47 ቤቶችን ማደስ ተችሏል። የትራፊክ አገልግሎቱም በጥሩ እየሄደ ነው። የደም ልገሳውም በተያዘለት ቀን የሚከናወን ይሆናል። የችግኝ ተከላውም እየተከናወነ ነው።

ከሞያ ነክ ስልጠናዎች ጋር በተያያዘም ምዝገባ ተካሂዶ ከሐምሌ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ትምህርቱ ይጀመራል። በወረዳው በኩልም በተለያየ መልኩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቱ በአግባቡ እንዲሄድ የማስተባበርና የድጋፍ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

የወጣት ካሊድንና ልዑለሥላሴን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተግባር ሌሎች ወጣቶችም እንደየሞያቸው፣ እውቀታቸውና እንዳላቸው ጊዜ ቢተገብሩት በርካታ ወገኖች ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም። በኅብረተሰቡ ዘንድ ለበጎ ፍቃድ ያለው አመለካከት ቢሻሻልና መንግሥትም ለዚህ ዘርፍ የሚያደርገው ድጋፍ ቢጠናከር ደግሞ ከሚታሰበው በላይ አገርንና ወገንን መጥቀም እንደሚቻል ሁሉንም ያስማማል።

በርግጥ በአሁኑ ጊዜ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በዓይነትም በብዛትም እየጨመረ መጥቷል። የወጣት ካሊድንና ልዑለሥላሴን የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም ለዚህ አንዱ ማሳያ ነው። የዘንድሮው የክረምት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም በአስራ አንድ የተለያዩ ዘርፎች በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እየተሰጠ ይገኛል። በመላው አገሪቱ የሚገኙ ከ19 ሚሊዮን በላይ ወጣቶችም ተሳትፈውበታል። በዚሁ የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም መንግሥትና ኅብረተሰቡ ሊያወጡ የሚችሉት 11 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ ይድናል ተብሎ ይጠበቃል።

አገልግሎቱ ሰኔ 15 ቀን 2014 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን እስካሁን ድረስ በአረንጓዴ አሻራ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ሰላም፣ መንገድ ደህንነት፣ ኮቪድ-19 መከላከልና ሌሎችም የጤና አጠባበቅ ሥራዎችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት ግንዛቤ መፍጠር ላይ ያተኮሩ ዘርፎች ላይ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት፣ የአረጋውያንና አቅመ ደካማ ቤት እድሳት፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን መከላከልና ግንዛቤ መፍጠርን ጨምሮ በሌሎች አስራ አንድ ዘርፎች ላይም ተመሳሳይ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

በዋናነት ደግሞ የወጣቶችን እርስ በእርስ ግንኙነቶች እንዲያጠናክሩና አጠቃላይ የወጣቶች ተሳትፎ የጎላ ሚና እንዲኖረው በሰላም ዙሪያ ያተኮሩ ግንኙነቶችም ተካሂደው አገልግሎቱ መስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል።

# የምድር በረከት

# ባህላዊ ወርቅ አምራቾችን በማመስገን ምርታማነትን ማሳደግ

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

ማዕድን ሚኒስቴር ባለፈው ሚያዝያ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው የ2014 በጀት አመት ዘጠኝ ወራት የስራ አፈጻጸም ሪፓርት የሀገሪቱ የማእድን ምርት ሀገራዊ ችግሮችን ተቋቁሞ ከፍተኛ እድገት እያሳየ መሆኑን መግለጹ ይታወሳል።ወርቅን ብቻ ብንመለከት በ2014 በጀት አመት ዘጠኝ ወራት 6ሺ 947 ኪሎ ግራም ወርቅ ለብሄራዊ ባንክ ቀርቧል፤ አፈጻጸሙ በሀገራዊ እቅዱ ከተያዘው እቅድ አንጻር ሲታይ 106 በመቶ ነው። ከ2013 በጀት አመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸርም የ12 በመቶ ብልጫ ታይቶበታል።

ወርቅ በስፋት ከሚመረትባቸው ክልሎች መካከል አንዱ በሆነው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከፍተኛ መጠን ያለው ወርቅ እንደሚመረት ከክልሉ የወጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በክልሉ ወርቅ እየተመረተ ያለው በባህላዊ መንገድ ብቻ ነው።

ክልሉ ሰሞኑን ለባህላዊ ወርቅ አምራቾችና አዘዋዋሪዎች የእውቅና መርሃ ግብር እና የማእድን ዘርፍ ሲምፓዚየም አካሂዷል፤ በመርሃ ግብሩ ላይ እንደተጠቆመውም፤ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወርቅን ጨምሮ የተፈጥሮ ሀብት የማልማት አቅሙ እየጨመረ መጥቷል። ለአብነትም በ2014 በጀት ዓመት ብቻ 22 ኩንታል ወርቅ ከክልሉ ወደ ብሄራዊ ባንክ ተልኳል፣ 514 ሺህ ቶን የከሰል ድንጋይ እና 164 ሺህ ቶን እምነበረድ በህጋዊ መንገድ ለምቷል።

በበጀት ዓመቱ ለ183 ወርቅ አምራቾች ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን፣ የወርቅ አምራቾች ብዛትም ከአምስት አመታት በፊት 86 ብቻ እንደ ነበር። የባህላዊ ወርቅ አምራቾች ማህበራት ቁጥርም ባለፉት ሶስት ዓመታት ከነበረበት 26 በ2014 በጀት ዓመት ወደ 234 አድጓል።

በመድረኩ የተገኙት የክልሉ ርእሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን እንዳሉት፤ ክልሉ ባለሃብቶችን በወርቅ፣ እምነበረድ፣ ከሰል ድንጋይ እና ሌሎችም ማዕድን ልማት ዘርፍ በስፋት እንዲሳተፉ አድርጓል።እያደገ የመጣውን የመካከለኛ እና አነስተኛ ወርቅ አምራች ማህበራት ቁጥር ማሳደግ እና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማደራጀት ሌላው የክልሉ መንግስት የትኩረት አቅጣጫ መሆኑን አስታውቀዋል።

ክልሉ ለረጅም ጊዜ በጸጥታ ችግር ሲፈተን መቆየቱንም ርእሰ መስተዳድሩ ጠቅሰው፣ በፈተና ውስጥ ዕድል በመፍጠር የተፈጥሮ ሃብቱን እያለማ እንደሚገኝ ተናግረዋል። የእውቀት እና የቁጠባ ባህል ማነስ እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብት ክብካቤ ማነስ የዘርፉ ፈታኝ ሁኔታዎች እንደሆኑ ገልጸው፤ በጥናት ላይ ተመስርቶ ችግሮችን ለመፍታት እንደሚሰራም ነው ያስታወቁት። በህገወጥ መንገድ ድንበር አቋርጦ የሚወጣ ወርቅ መኖሩን የጠቀሱት ርእሰ መስተዳድሩ፣ ችግሩን ለመፍታት የተጀመሩ እርምጃዎች እንደሚጠናከሩ መግለጻቸውን የኢዜአ ዘገባ ያመለክታል።

የክልሉ ማዕድን ልማት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ናስር መሃመድ በበኩላቸው ባለፉት ሶስት አመታት የወርቅ እና የሌሎች ማዕድናት ምርት በከፍተኛ መጠን መጨመሩን አስረድተዋል። የማዕድን ምርት ሊጨምር የቻለው መንግስት ባለፉት ሶስት አመታት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት መሆኑን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ውጤቱ እንዲቀጥል ህብረተሰቡ ሰላሙን እንዲጠብቅ መጠየቃቸውን የኢዜአ ዘገባ ያመልክታል።

የክልሉ የማዕድን ልማት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ናስር መሀመድ በተለይ ለአዲስ ዘመን በስልክ እንዳሉት፤ የእውቅና ፕሮግራሙ አላማ ባህላዊ የወርቅ አምራቾችና አዘዋዋሪዎች የወርቅ ምርታማነትን የማሳደግ ጥረታቸውን ይበልጥ እንዲያጠናክሩ ለማበረታታት ነው። በባህላዊ መንገድ እያመረቱ 22 ኩንታል ወርቅ ለብሄራዊ ባንክ ማቅረብ መቻል ቀላል አይደለም። ክልሉ ካለው እምቅ የወርቅ ሀብት አኳያ ብዙ ወርቅ ማምረት እንደሚጠበቅ ለማስገንዘብ ተሰርቷል። የአደረጃጀቱ ነገር ጥሩ ሆኖ የሚመረተው ወርቅ ግን በቂ አለመሆኑ ላይ መልእክት ለማስተላለፍ ተሞክሯል፤ ማህበራቱ ገና ብዙ ስራ እንደሚጠበቅባቸው ተጠቁሟል።

በመድረኩ ከአምራች ማህበራት 15 እንዲሁም ከወርቅ አዘዋዋሪዎች 15 የሚሆኑት ሽልማትና ሰርተፍኬት እንደተበረከተላቸውም ዋና ዳይሬክተሩ ይገልጻሉ። ለሽልማት የበቁት አዘዋዋሪዎች ለብሄራዊ ባንክ ባስገቡት የወርቅ መጠን ሲሸለሙ፣አምራቾቹ ደግሞ በፈጠሩት ሀብትና የስራ እድል ልክ ተሸላሚ ተደርገዋል።

ከዚህ ቀደም በሀገር ደረጃ ይህን አይነት መድረክ የተካሄደ ቢሆንም፣ በክልል ደረጃ ሲደረግ ግን ይህ የመጀመሪያው ነው ይላሉ። ያለፈው መድረክ ለውጥ ማሳየቱን ጠቅሰው፣ አምና 21 ኩንታል፣ ዘንድሮ ደግሞ 22 ኩንታል ወርቅ ማምረት መቻሉን ጠቅሰዋል። ከአምስት አመት በፊት ከ50 ኪሎ ግራም የማይዘል ወርቅ ነበር የሚመረተው ሲሉ ያስታውሳሉ።

‹‹ይህን መድረክ አጠናክረን መቀጠል ከቻልን የበለጠ ለውጥ ማምጣት አንደምንችል ተረድተናል›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ አምራቾቹም በመሸለማቸው መደሰታቸውን፣ ጥሩ የማበረታቻ መንገድ አንደ ሆነም በመጥቀስ ምስጋና ለክልሉ ማቅረባቸውን አስታውቀዋል። በመድረኩ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ተገኝተዋል፤ መድረኩ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ሁሉም አካላት ማስገንዘባቸውን ዋና ዳይሬክተሩ ገልጸው፣ ጥሩ ለሰራ ምስጋና በማቅረብ ስራውን እንዲያጠናክር ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት ፤ የክልሉን የወርቅ ማዕድን እምቅ አቅምን በተመለከተ ይህን ያህል መጠን የወርቅ ሀብት አለ ተብሎ የተጠና ነገር የለም። በክልሉ ሶስቱም ዞኖች እና አንድ ልዩ ወረዳ የወርቅ ማዕድን ይገኛል።በባህላዊ መንገድ እየተካሄደ ባለው የወርቅ ልማት በርካታ የክልሉ ነዋሪዎች በማህበራት ተደራጅተው እየሰሩ ናቸው፤ የማምረቱ ስራ ግን ኋላ ቀር ሲሆን፣ ቁፋሮው በእጅ ነው የሚካሄደው። ወርቅ የሚገኝበትን ድንጋይ አምራቾቹ የሚፈለፍሉትም እንዲሁ በኋላ ቀር መሳሪያ ነው። ከዚያም ድንጋዩ በወፍጮ እየተፈጨ በውሃ እየታጠበ ወርቁ እንዲወጣ ይደረጋል።

ይህን አመራረት ለማዘመን የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙም ነው ዋና ዳይሬክተሩ የሚናገሩት። ኩባንያዎች የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን እያቀረቡ መሆናቸውን፣ ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር እንደ ወፍጮ እና መቆፈሪያ ያሉ መሳሪያዎች ዘመናዊነት የተላበሱ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ያብራራሉ። የማዘመን እገዛው በወፍጮ በመቆፈሪያና በመሳሰሉት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ አመራረቱ በቴክኖሎጂ መታገዝ መጀመሩን ተከትሎ ምርቱም እየጨመረ ይገኛል ብለዋል። ከዚህ ቀደም በጣም ውስን ወርቅ ይመረት እንደነበር ተናግረው፣ ያም ከአሁኑ ምርት አንጻር ሲታይ ዜሮ እንደማለት መሆኑን ያስታውሳሉ።

መረጃዎች አንደሚጠቁሙት፤ በወርቅ ማምረቱ ባህላዊ አምራቾችና ኩባንያዎች እየተሳተፉ ሲሆን፣ የባህላዊ አምራቾቹ ድርሻ ከፍተኛ ነው። በኢትዮጵያ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች በወርቅ ማውጣት ስራ ተሰማርተዋል። ከእነዚህ መካከልም ባህላዊ ወርቅ አምራቾች ሰፊውን ድርሻ ይይዛሉ። በየአመቱ ለውጭ ገበያ ከሚቀርበው የወርቅ ምርት ከ60 በመቶ በላይ የሚሆነው የሚመረተው በባህላዊ መንገድ ነው።

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ደግሞ ከፍተኛ መጠን ያለው ወርቅ በባህላዊ መንገድ ብቻ እያመረተ ነው። በርካታ አባላት ያሏቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ማህበራትም ይገኛሉ። ይህን አቅም በማዘመን የወርቅ ምርታማነትን ማሳደግ እንደ ሀገር በማዕድን ዘርፍ ለማከናወን መስራት ይገባል። የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልም ይህን እያደረገ ይገኛል።

እንደ አቶ ናስር ገለጻ፤ በክልሉ የወርቅ ምርታማነትን ለማሳደግ ብዙ እቅዶች አሉ፤ ክልሉ የልማት ድርጅት አቋቁሟል፤ የተለያዩ የልማት ድርጅቶችም አሉ፤ እነዚህ አካላት የተሻለ ቴክኖሎጂ እንዲያቀርቡና በባህላዊ መንገድ የሚመርትበትን መንገድ በማዘመን የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን ይሰራል። በእዚህ በኩል በጋራ ለመስራት ነው እየተሞከረ ያለው።

> **በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ወርቅ በባህላዊ መንገድ የሚመረት ሲሆን፣ አምና 21 ኩንታል፣ ዘንድሮ ደግሞ 22 ኩንታል ወርቅ ማምረት ተችሏል፡፡ ከአምስት አመት በፊት ከ50 ኪሎ ግራም የማይዘል ወርቅ ነበር የሚመረተው**

በግብይቱም ላይ በሰጡት ማብራሪያ ለወርቅ አዘዋዋሪዎች ፈቃድ እየተሰጠ እንደሚሰራ ነው የተናገሩት፤ እነሱ ወርቁን በአሶሳ በብሄራዊ ባንክ ውክልና ለተሰጠው አካል ያቀርባሉ ይላሉ። ከዚህ በመለስ ግን በግብይቱ ላይ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ስለመኖራቸውም ይጠቁማሉ።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ክልሉ ከሱዳንና ደቡብ ሱዳን ጋር ይዋሰናል፤ ወርቁ የሚመረተው በአብዛኛው በእነዚህ ጠረፍ አካባቢዎች ነው። በግብይቱ ላይ ጥቁር ገበያውና ኮንትሮባንዲስቶች ችግር እየፈጠሩ ናቸው። በእነዚህ ድንበሮች አካባቢ የወርቅ ህገ ወጥ ንግድ ይስተዋላል። ይህን ችግር ለመፍታት ግብረ ሀይል ተቋቁሞ በቁጥጥርና ክትትል እየተሰራ ይገኛል። ችግሩን የመፍታቱ ስራ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራን በስፋት ይጠይቃል።

የፌዴራል መንግስት የማዕድን ፓሊሲ እያዘጋጀ ነው፤ ይህም የማዕድን ልማቱንና ግብይቱን መምራት የሚያስችል ነው፤ እኛ ድንበር አካባቢ እንደመገኘታችን እንደ ክልል ሁሉም የጸጥታ ተቋማት በግብረ ሀይል ውስጥ ይሰራሉ። መከላከያ፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ ጉምሩክ ከኛ ጋር በግብረ ሀይል አብረን እየሰራን ነው። አስፈላጊውን ቁጥጥር እንዲያደርጉ ሁሌም አብረን እንመክራለን። ጠንካራ ፍተሻ እየተደረገም ይገኛል። ይህም ህገወጥ የወርቅ ዝውውሩን ለመቆጣጠር አስተዋጽኦ እያደረገ ነው።

ይህ ሀብት የአምራቹን ህይወት እንዲቀይር፣ የክልሉን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እንዲያሳድግ እየተሰራ መሆኑንም ነው ዋና ዳይሬክተሩ የጠቆሙት። ይህ ህብረተሰብ ወርቅ ላይ ተቀምጦ የሚቸገር ነው ሲሉ ገልጸው፣ እኛ ማዕድኑ የህብረተሰቡን ህይወት እንዲቀይር ምኞታችን ነው፤ አቅሙ ያላቸው ባለሀብቶች፣ ቴክኖሎጂው ያላቸው አካላት ወደ ክልሉ መጥተው ከህብረተሰቡ ጋር እንዲሰሩ እንፈልጋለን ሲሉም አስታውቀዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ናስር ገለጻ፤ የባህላዊ አምራቾቹ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ እንደ ክልል ሰፊ ስራ እየተሰራ ነው። በኩባንያ ደረጃ በዘመናዊ መንገድ በክልሉ ወርቅ እየተመረተ አይደለም። ባለሀብቶች በወርቅ ማምረት ስራ ለመሰማራት ቦታዎችን ከአመታት በፊት ቢወስዱም ፣ ባለፈው ስርአት ቦታ መያዝ እንጂ ማልማት ውስጥ መግባት ብዙም አይታይም ነበር። አሁን ባለሀብቶቹ ወደ ልማቱ አንዲገቡ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ናቸው። ክልሉ እያደረገ ያለውን ጥሪ ተከትሎም ሌሎች ባለሀብቶች ወደ ክልሉ እየመጡ ይገኛሉ።

እንደ ሀገር ሰላምና ደህንነቱ ከተረጋጋ የማዕድን ሀብቱ የሚለማበት አቅጣጫ እየተቀመጠ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ከአራት አመት በፊት ማዕድን ብዙም ትኩረት የተሰጠው አልነበረም ይላሉ፤ አሁን ግን ከቡና ቀጥሎ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ተጠቃሹ መሆን መቻሉን ነው የተናገሩት።

አምራቹ ከወርቅ ምርቱ የሚያገኘውን ሀብት በአግባቡ እንዲጠቀምበት፣ ህይወቱን እንዲቀይርበት ወደ ተሻለ ማምረት ስራ መግባት እንዲችል ለማድረግ ቁጠባ ላይ እየተሰራ መሆኑንም ይገልጻሉ። ከወርቅ የሚገኘው ብር የማያልቅ አርጎ የመጠቀም ጎጂ ባህል አለ ሲሉ ገልጸው፣ ይህን ባህል ማስቀረት ብዙ ስራ እንደሚጠይቅ ነው የተናገሩት።ይህን ስራ የክልሉ ማዕድን አጀንሲ ብቻውን ሊሰራው እንደማይችልም አስታውቀዋል፤ ስልጠና በተከታታይ እንዲሰጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተነጋግረናል፤ የቁጠባ ባህልን ለማሳደግ ከተለያዩ ተቋማት ጋር እየመከርን ነው። በትምህርትና ስልጠና ግንዛቤ ለማስጨበጥ እየተሞከረ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል።

ቁጠባ አስፈላጊ ነው። ይህ ማለት ግን ቁጠባ ጨርሶ የለም ማለት አይደለም፤ ከነበሩበት ሁኔታ አኳያ ሲታይ ትልቅ መሻሻል አለ። የቁጠባን ባህል በማሳደግ በኩል እየተሰራ ነው። በማዕድን ሚኒስቴር በኩልም ግንዛቤ በማሳደግ በኩል እየሰራ ነው። በሶስት አመታት ውስጥ ያልነበረ ነገር ማምጣት ተችሏል።

‹‹ለውጡን ለማበላሸት የሚደረግ ሙከራ አለ፤ በጸጥታ በኩል ገባ ወጣ የሚል ችግርም ይስተዋላል›› የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ይሄ የአምራቹ ትልቁ ተግዳሮት መሆኑን ነው የጠቀሱት። ተግዳሮቱ አምራቾቹ ወርቅ የማምረቱን ስራ ያዝ ለቀቅ እንዲያደርጉት እያስገደዳቸው ነው ይላሉ። መንግስት በጸጥታ ማስፈኑ በኩል ጥሩ እየሰራ ነው የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ይህ ችግር ይፈታል የሚል እምነት አላቸው። ሁለተኛው ችግር በቴክኖሎጂ በኩል ለሚቀርብ ጥያቄ በቁጠባዎች በኩል ፈጣን ምላሽ አለመስጠታቸው ነው።በእዚህ ላይ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል። በተረፈ ግን ሁኔታዎች በጥሩ ደረጃ ላይ ናቸው ብለዋል።

በአስር አመቱ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መሪ እቅድ ላይም የማዕድን ዘርፍ ከአምስቱ የእድገት ማእዘኖች አንዱ እንደመሆኑ ክልሉ ከፍተኛ መጠን ያለው ወርቅ እያመረቱ ለሚገኙት ለባህላዊ ወርቅ አምራቾች የሰጠው እውቅናና ማበረታቻ ተገቢና ወቅታዊ ነው። ለአምራቾቹ የሚደረግ የትኛውም ድጋፍ አምራቾቹን ከማትጋት ባሻገር እንደ ሀገር እና ክልል ከወርቅ ማዕድን ለማግኘት የተያዘውን እቅድ ለማሳካት የበኩሉን ሚና ይጫወታል።የባህላዊ አምራቾችን የማምረት አቅም በቴክኖሎጂና በስልጠና በማሳደግ ከዘርፉ የሚጠበቀውን ምርታማነት ማሳደግም ይገባል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የትዝታ ቆፈን

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የህይወት ውበት ትዝታና ተስፋ ናቸው። ነፍስ በትዝታና በተስፋ መርፌ የተሰፋች ይመስለኛል። ደግሞም ተሰፍታለች፣ ከጠዋት እስከ ማታ የማረምመው አርምሞ የነፍስ ባለቀለም እንጉርጉሮ ከመሆን ሌላ ምን ሊሆን ይችላል? ህይወት ከፊት ትዝታ ከኋላ ተስፋ ባይኖራት ምን እንደምትመስል ሳስብ የሌለ እጨነቃለሁ።

መኝታ ክፍሌ ውስጥ ነኝ..አልጋዬ መከዳ ላይ ቁጭ ብዬ አስባለሁ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ካጠናቀኩ አስራ አምስት ዓመታት ተቆጠሩ..እንደ እስቅያስ በልጅነት እድሜዬ ላይ አስራ አምስት ዓመታትን ጨመርኩ። በትዝታ የተሰፉ አስራ አምስት የናፍቆት ዓመታት እንደ ጅረት በላዬ ላይ ፈሰሱ። ሰው የዘመን ወንዝ ነው..ነፍስ የጊዜ ውቅያኖስ ናት። በላዬ ላይ የተጫነውን የትዝታ ቀንበር አዝዬ አስራ አምስት ዓመታትን ወደ ኋላዬ አረምማለሁ። የህይወቴ ደማቋ ፊደል መባ ጋ እስከደርስ ድረስ የትዝታ ተጓዥ ነኝ። ነፍሴ ላይ ነግሳ አበሳዬን እስክታስረሳኝ ድረስ እዛና እዚህ እዳክራለሁ። ነፍስ አውቄ ጉርምስና በተሰማኝ ሰሞን የተነካካሁት ከመባ ጋር ነው። መባ ከልጅነት ወደ ጉርምስና በተሸጋገርኩ ማግስት የተዋወኳት ልጅ ናት። ልጅነቴን ሳስብ፣ ጉርምስናዬን ሳስታውስ ቀድማ አእምሮዬ ውስጥ የምትፈጠረው መባ ናት። ዛሬ ላይ ያን ስሜት ማንም አልሰጠኝም። ባሳለፍኳቸው አስራ አምስት ዓመታት ውስጥ ከተለያዩ ቆንጆና ዘመነኛ ሴቶች ጋር ወዳጅነትን ፈጥሬያለሁ እንደ መባ ነፍሴን በደስታ ያቃተተኝ ሴት ግን የለም።

ፍቅር ድሮና ዘንድሮ ሰማይና ምድር ነው። ፍቅር የልብ ሰማይ ነው..ፍቅር የነፍስ ምድር ነው። አምላክ ዙፋኑን የዘረጋው በፍቅር ሰማይ ላይ ነው። በእውነት ምድር ላይ ነው። ያ የፍቅር ሰማይ፣ ያ የእውነት ምድር ልብ ነው። ፍቅር የነፍስ ምድር ነው። በልብ ሰማይ ላይ ከዋክብቶች ደምቀው የሚያበሩት በህይወት ጠዋት ላይ ነው። በህይወት ከሰዐት ላይ ቆሜ ዛሬም ድረስ የማዜመው የማለዳ ዜማዬን ነው። መባ ያለችበትን ያ የጠዋት ድርሳኔን። ትዝ ይለኛል.. አስረኛ ክፍል ነበርኩ ለአዲስ ዓመት የተገዛልኝን አዲስ ስኒከር ጫማ ተጫምቼ ወደ ክፍል እገባለሁ። ጫማው ከተገዛልኝ ከጳጉሜ ሶስት ከሩፋኤል ቀን ጀምሮ አይኖቼ ከዛ ነጭ ጫማ ላይ ተነቅለው አያውቁም ነበር። መሬት መሬት እያየሁ ነበር የምሄደው። ከመባ ጋርም የተዋወቅነው በዛ ስኒከር ጫማ ሰበብ ነበር። ያን ቀን ብርቅ የሆነብኝን ጫማዬን እያየሁ ወደ ክፍል ስገባ ከአንዲት ሴት ጋር ተጋጨሁ። ግጭታችን ሀይለኛ ስለነበር ሁለታችንም መሬት ላይ ወደቅን.. አወዳደቃችንን ዛሬ ላይ ሳስበው የፍቅር አምላክ እጅ ያለበት ይመስለኛል። ከዛ በኋላም ሆነ ከዛ በፊት ምድር ላይ እንደዛ ተቃቅፈው የሚወድቁ ወንድና ሴት ስለመኖራቸው እጠራጠራለሁ። ብቅ ብቅ ያሉ ጡቶቿን ተንተርሼ ደረቷ ላይ..ራሴን አገኘሁት። አፌ አፏ ላይ እንደተደፋ ያወኩት ዘግይቼ ነበር። ባጋጣሚ ቢሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ ከንፈሬ ከሴት ከንፈር ጋር የተሳሳመው በዛ ጫማ ጦስ ነው። እንደምንም ራሴን ከደረትና ከጡቷ ላይ አንስቼ ወደ ክፍል ተንደረደርኩ። ለካ የክፍላችን ተማሪ ነበረች..። እኔም እሷም ዓመቱን ሙሉ በሀፍረት አሳለፍን። ምንም ሳንባባል ዓመቱ አለቀ። ወንድነቴ በመባ ከንፈር ተሟሸ። ከንፈር ምን ምን እንደሚል ለመጀመሪያ ጊዜ ያጣጣምኩት ያኔ ነው እላለሁ። ያ ጫማ..ያ አጋጣሚ...ያ አዲስ ዓመት ሁሌም ይናፍቁኛል። በህይወቴ እንደዛ አይነት አዲስ ዓመት አሳልፌ አላውቅም። ያ አዲስ ዓመት ዛሬም ከነሙሉ ግርማ ሞገሱ ይታወሰኛል።

አስራ አንደኛ ክፍል አብረን ተመደብን፣ በጣም የሚገርመው ደግሞ አስራ ሁለተኛ ክፍልም አንድ ላይ መሆናችን ነው። በዛች የተረገመች አጋጣሚ አፍራ ይሁን እንጃ ሶስት ዓመት አላወራንም። ክፍል ውስጥ ከሁሉም ወንዶች ጋር ስታወራ ከኔ ጋር ብቻ አታወራም። ልቤ የመጀመሪያህ እያለ ያወራኛል። ነፍሴ ሳቋን ትናፍቃለች..ግን ትሸሸኛለች። ዳግም የማንገናኝበት ጊዜ ከፊታችን መጣ። አንድ ማለዳ ልቤ የሆነ ነገር አለኝ..ልቤን አደመጥኩት። ልብ የእውነት ስፍራ እንደሆነ ያን ቀን ነው የተረዳሁት። የልቤን እውነት ይዘው እግሮቼ ወደ አንድ ቦታ መሩኝ..ከዛ በፊት ወደዛ ቦታ ሄጄ አላውቅም ነበር.. ዛሬ ለምን እንደሄድኩ የገባኝ መናን በዛ ሰዋራ ስፍራ ብቻዋን ተቀምጣ ሳያት ነበር። ፊት ለፊት ተፋጠጥን.. ምን ማለት እንዳለብኝ ግራ ገባኝ። በአእምሮዬ ውስጥ ሁለት ሀሳቦች ተጻነሱ። አንደኛው..ይሄ መባን በተመለከተ በህይወትህ ዳግመኛ የማታገኘው አጋጣሚ ነው አውራት ይለኛል..ሌላኛው ደግሞ ሌላ ይለኛል። ዛሬ ላይ በማላስታውሰው ውስጣዊ ሀይል ተጠጋኋት..እጄ ላይ ደብተር ይዤ ነበር..ዛሬ ክላስ አልገባም ጻፊልኝ ብዬ ደብተሬን ወርውሬላት መልስ እንኳን ሳልጠብቅ ከፊቷ ተሰወርኩ። እንደዛ ቀን ጠዋት ነቅቼ አላውቅም..ነግቶ ደብተሮቼን ለማየት የቸኮልኩትን አቸኳኮል ለምንም ቸኩዬ አላውቅም። ጠዋት ክፍል ስገባ ሳልጠይቃት ደብተሬን አምጥታ ሰጠችኝ..ጽፋልኝ ነበር። አመሰግናለው ሳልላት የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ደርሶ ተለያየን።

ከአልጋዬ መከዳ ላይ ሆኜ መባ የጻፈችልኝን እያየሁ ብዙ ቆየሁ። ከደብተሬ ገጽ ላይ ከጽሁፎቿ መሀል አገኞት ይመስል ፈለኳት። ጽሁፏ ያስቃል... መባ ጽሁፍ አትችልም። ከዛ ውበት፣ ከነዛ ጣቶች መሀል እንዲህ አይነት አስጠሊታ ጽሁፍ መውጣቱ ሁሌም ያስደንቀኛል። መባን እያሰብኩ እጄ የገባውን አንዱን ገፅ ሳገላብጥ ሊደበዝዝ ያለ አንድ ስልክ ቁጥር ደብተሬ ገጽ ላይ ተጽፎ አየሁ። ቁጥሩን በደንብ አየሁት አላውቀውም። ላስታውሰው ብዙ ሞከርኩ ግን አልመጣልኝም። ግን አላረፍኩም..ሳላስበው አስባለሁ። ወደ ኋላ አስራ አምስት ዓመት ተራምጄ የክፍል ጓደኞቼን አስሳለሁ። አንዳንዶቹ ታወሱኝ አንዳንዶቹ ግን ጠፉብኝ። መባ ግን ያው እንደ ድሮዋ ዛሬም በነፍሴ ቦታ ላይ አለች። የሆነ ጥርጣሬ አእምሮዬ ውስጥ ሰተት አለ። ስልኩ የመባ መሰለኝ..ደብተሬን ለመጨረሻ ጊዜ ለሰው የሰጠሁት ለእሷ ነበር። ከዛ በኋላ መልቀቂያ ፈተና ስለወሰድን ብዙ አልቆየንም። ስልኩ የመባ ከመሆን ውጪ የማንም እንደማይሆን አእምሮዬ ለመቶኛ ጊዜ ነገረኝ። ግን አእምሮዬን አላመንኩትም..የእሷ ከሆነ በደስታ አብዳለሁ..አለም ይጠበኛል። የእሷ በሆነ ስል ተመኘሁ። ትዝታዬን ተከትሎ ነፍሴ በደስታ ከልቤ ውስጥ ልትወጣ ምንም አልቀራትም ነበር። ስልኩ የመባ ስለመሆኑ እርግጠኛ ሆንኩ። ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ የመባን ድምጽ ልሰማው እንደሆነ ሳስብ የተደሰትኩትን መደሰት አትጠይቁኝ።

ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ እየተደነኩና እየተገረምኩ ወደ ማላውቀው ስልክ ቁጥር ላይ ደወልኩ። ከነፍሴ ወደ ፊቴ የሚፈስ የሳቅ ጎርፍ ይታየኛል። ምን ማለት እንዳለብኝ እያሰብኩና ከንፈሬን በምላሴ እየላስኩ ጠበኩ..

ልቤ ይደልቃል..
ቀጭን ሞልቃቃ ድምጽ በአይኔ ላይ
ያንዣብባል..

ብዙ አልቆየሁም..ጆሮዬ አንድ መርዶ አደመጠ ‹ይህ ቁጥር አይታወቅም፣ እባኮ የጥሪ ማዕከሉን ያናግሩ› የሚል። ቴሌ ቅስሜን ሰበረው..

# ዓለም አቀፍ

## በናይጄሪያዋ አቡጃ እስር ቤት ላይ በተፈጸመ ጥቃት ከ400 በላይ እስረኞች አመለጡ

በናይጄሪያዋ ዋና ከተማ አቡጃ ውስጥ በሚገኝ አስር ቤት ላይ የተፈጸመን ጥቃት ተከትሎ ከ400 በላይ አስረኞች ማምለጣቸውን የአገሪቱ ባለሥልጣናት አስታወቁ።ማክሰኞ ሌሊት እስር ቤቱን ኢላማ ያደረገው ጥቃት መፈጸሙን ተከትሎ በጥቃቱ አራት አስረኞች፣ አንድ የእስር ቤቱ ጠባቂ እና በርካታ ጥቃት ፈጻሚዎች መገደላቸውን ባለሥልጣናቱ አሳውቀዋል።

ኢስላማዊ ታጣቂዎች ይህንን ጥቃት ሳይፈጽሙ እንዳልቀሩ የተጠረጠረ ሲሆን፣ በርካታ ቁጥር ያላቸው የቡድኑ አባላት ከእስር ቤቱ ሳያመልጡ እንዳልቀሩ ይታመናል።ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በናይጄሪያ ከሚገኙ እስር ቤቶች ከ5 ሺህ በላይ ታሳሪዎች የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ተከትሎ ማምለጣቸው ይነገራል።ከዋና ከተማዋ ወጣ ብሎ በሚገኘው መካከለኛ ጥበቃ በሚደረግለት የኩጄ እስር ቤት ላይ ማክሰኞ ዕለት ጥቃቱ ሲፈጸም በአቅራቢያው ከባድ ፍንዳታና የተኩስ ድምፅ ተሰምቷል።

“በመጀመሪያ የተኩስ ድምፅ ስንሰማ ታጣቂዎች ዘረፋ ፈጽመው ሊሆን ይችላል ብለን ነበር” ሲል አንድ የአካባቢው ነዋሪ ለኤኤፍፒ ዜና ወኪል ተናግሯል።”ከተኩሱ በኋላ ፍንዳታ ተከተለ። ከዚያም በተደጋጋሚ ፍንዳታ ተሰምቷል።”በጥቃቱ አራት እስረኞች የተገደሉ ሲሆን፣ ሌሎች 16 ደግሞ የመቁሰል ጉዳት እንደደረሰባቸው የናይጄሪያ የማረሚያ ቤቶች አገልግሎት አስታውቋል።

ጥቃቱ በተፈጸመበት ወቅት በርካታ ቁጥር ያላቸው ተጠርጣሪ ታጣቂዎች እና ፖለቲከኞችን ጨምሮ ከፍተኛ ወንጀል ፈጽመዋል የሚባሉ ግለሰቦች በእስር ቤቱ ውስጥ ነበሩ። ነገር ግን የማረሚያ ቤቶች ባለሥልጣናት እንዳሉት ከእነዚህ መካከል ያመለጡ እንደሌሉ ተናግረዋል።ጥቃቱ ሲፈጸም በእስር ቤቱ ውስጥ 1 ሺህ የሚሆኑ እስረኞች እንደነበሩ ባለሥልጣናት አመልክተዋል። ጥቃቱን ተከትሎ ሁሉም በሚባል ደረጃ ከአስር ቤቱ አምልጠው የነበረ ቢሆንም 443ቱ መልሰው ተይዘዋል።

የናይጄሪያ የመከላከያ ሚኒስትር ባሺር ማጋሺ



በናይጄሪያ ዋና ከተማ አቡጃ ጥቃቱ የተፈጸመበት እስር ቤት አንድ ክፍል

ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት፣ ጥቃቱ በታጣቂው ቦኮ ሃራም ቡድን ሳይፈጸም እንዳልቀረ አመልክተዋል። በዚህም በአስር ላይ የነበሩ 64 ኢስላማዊ ታጣቂዎች ማምለጣቸውንም ጨምረው ገልጸዋል።“አንዳቸውም በእስር ቤቱ ውስጥ የሉም፣ አምልጠዋል” ብለዋል ሚኒስትሩ፥

ኢስላማዊ መንግሥት ወይንም አይኤስ የሚባለው ቡድን አካል ነኝ የሚለውና በምዕራብ የአፍሪካ ክፍል የሚንቀሳቀሰው የቦኮ ሃራም ቡድን አጋር፣ በእስር ቤቱ ላይ ለተፈጸመው ጥቃት ኃላፊነቱን በመውሰድ በርካታ አስረኞችን ማስለቀቁን ገልጿል።የናይጄሪያው ፕሬዚዳንት ሙሐማዱ ቡሃሪ የአገሪቱ የደኅንነት ተቋማት የመረጃ ሥርዓት ደካማነትን በማንሳት ለጥቃቱ መከሰት ምክንያት ነው ሲሉ ወቅሰዋል።

ፕሬዚዳንቱ ጨምረውም ለእስር ቤቱ ይደረግ በነበረው ጥበቃ ላይ ጥያቄ አንስተው፣ ስለተፈጸመው ጥቃት “አጠቃላይ ሪፖርት” እንዲቀርብላቸው አዘዋል።

በአገሪቱ በትጥቅ የተደገፉ ጠላፊ ወንጀለኞችና ታታቂ ቡድኖች በሚፈጽሟቸው ጥቃቶች ሳቢያ የፕሬዚዳንት ቡሃሪ መንግሥት እየተስፋፋ ያለውን የደኅንነት ስጋት ሊቆጣጠር አልቻልም በሚል እየተጠናከረ የመጣ ትችት እንደሚቀርብበት የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## የብሪታኒያው ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ስልጣን ለመልቀቅ ወሰኑ

የብሪታኒያው ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ስልጣን ለመልቀቅ መወሰናቸውን መገናኛ ብዙሃን ዘገቡ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ስልጣን ለመልቀቅ የወሰኑት ባለፉት ሁለት ቀናት ከ50 በላይ የመንግሥታቸው ሚኒስትሮች እና የስራ ሀላፊዎች ስልጣን መልቀቃቸውን ተከትሎ ነው ተብሏል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከወግ አጥባቂው ፓርቲ መሪነታቸው ለመልቀቅ የተስማሙ ሲሆን፥ ቀጣዩ የፓርቲው መሪ እስከሚታወቅ ድረስ በጠቅላይ ሚኒስትርነታቸው እንደሚቆዩም ተገልጿል። እሳቸው ግን ለተወሰኑ ወራት በጠቅላይ ሚኒስትር የመቆየት ፍላጎት እንደነበራቸው ነው የሚነገረው።የተቃዋሚው ሌበር ፓርቲ መሪ ኬይር ስታርመር የጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሳኔ



ለሀገሪቱ መልካም ዜና ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የብሪታኒያው ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ከካቢኔ ሚኒስትሮቻቸውና ከምክር ቤት አባላት ድጋፍ ሳያገኙ በመቅረታቸው ከወግ አጥባቂው ፓርቲያቸው መሪነት ሊለቁ ነው።ለፓርቲው መሪነት የሚደረገው ፉክክር በቅርቡ የሚደረግ ሲሆን፣ በቀጣይ ዓመት ጥቅምት ወር ላይ ደግሞ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሰየማል።እስከዚያው ድረስ ግን ቦሪስ ጆንሰን በአገሪቱ የጠቅላይ ሚኒስትር መንበር ላይ ይቀጥላሉ።

ጆንሰን በአመራራቸው ላይ በርካታ ትችቶች ሲቀርብባቸው ቆይቶ በርካታ ባለሥልጣኖቻቸው በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ከለቀቁ በኋላ ነው ከዚህ ውሳኔ ላይ የደረሱት።ከእነዚህም መካከል ቻንስለር ናዲም ዛሃዊን ጨምሮ ከፍተኛ ካቢኔ አባሎቻቸው “በክብር የሥልጣን መንበራቸውን እንዲለቁ” ለጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ጥያቄ አቅርበው ነበር።ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዚህ ውሳኔ ላይ የደረሱት ሪሺ ሱናክን ጨምሮ በርካታ ሚኒስትሮቻቸው አመራራቸውን በመቃወም በ48 ሰዓታት ውስጥ በፈቃዳቸው ሥልጣን ከለቀቁ በኋላ ነው።

በተመሳሳይ ቦሪስ ጆንሰን ሥልጣን እንዲለቁ የቀረበላቸውን ጥያቄ እስከ ሐሙስ ረፋድ ድረስ ሳይቀበሉት ቆይተው፣ የፓርላማ አባሎቻቸውን ድጋፍ ማግኘት ሳይችሉ በመቅረታቸው በመጨረሻ ወስነዋል።ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን በፓርቲያቸው ውስጥ የተደረገውን ውድድር በማሸነፍ በ2019 ነበር ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት። ከአምስት ዓመት በኋላ በከፍተኛ የድምጽ ብልጫም ምርጫ ማሸነፋቸው ቢቢሲ አስታውሶ ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንና ፌስቡክ ገጾችን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ዓርብ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የኦሊምፒክ ስህተት የታረመበት የዓለም ቻምፒዮና አትሌቶች ምርጫ

ቦጋለ አበበ

በአሜሪካ ፖርትላንድ ኦሪገን የሚካሄደው የዘንድሮው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከሳምንት ያልበለጠ ጊዜ ይቀረዋል። ኢትዮጵያን በተለያዩ ርቀቶች በመወከል የሚወዳደሩ ስመ ጥር አትሌቶችም ባለፉት በርካታ ሳምንታት በዝግጅት ላይ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ በኦሊምፒክና በዓለም ቻምፒዮና ስኬታማ በሆነችባቸው የ5 እና 10ሺ ሜትር ውድድሮች በኦሪገኑ ቻምፒዮናም ውጤት ታስመዘግብባቸዋለች ተብሎ ከሚጠበቁ ውድድሮች ዋናዎቹ ናቸው። ለዚህም ኢትዮጵያ በርቀቶቹ የብቃታቸው ጣራ ላይ የሚገኙና የዓለም ኮከብ የሆኑ በርካታ አትሌቶች በሁለቱም ጾታ እንዳላት በውድድር አመቱ በተለያዩ አጋጣሚዎች መታዘብ ተችሏል። እነዚህ ከዋክብት አትሌቶች በኦሪገኑ ቻምፒዮና ኢትዮጵያን እንዲወክሉ ተመርጠው እየተዘጋጁም ይገኛሉ። የ5 እና 10ሺ ሜትር በተለይም ወንድ አትሌቶች አመራረጥን በተመለከተ ፌዴሬሽኑ መጀመሪያ የመለመላቸው አትሌቶች ላይ ጥርጣሬዎች የነበሩ ቢሆንም ከትናንት በስቲያ ይፋ ባደረገው የመጨረሻ ዝርዝር ላይ በርካቶችን ያሳመነ ለውጥ አድርጓል። ይህም እንዳለፈው ቶኪዮ ኦሊምፒክ ኢትዮጵያ ወርቅ የማስመዝገብ አቅሙና ብቃቱ ያላቸው አትሌቶች ይዛ እነሱን በአግባቡ ባለመጠቀም እንደገጠመው ዓይነት የውጤት ቀውስ እንዳይደገም የነበረውን ስጋት ማስቀረት ችሏል።

በአትሌቲክስ ታሪክ የ10ሺ እና 5ሺ ሜትር ውድድሮች ኢትዮጵያ ስኬታማ የምትሆንባቸው ፉክክሮች ብቻ ሳይሆኑ በአትሌቲክስ ባለፉት በርካታ አመታት ገናና ስም እንዲኖራት የአንበሳውን ድርሻ የተወጡ ናቸው። ያ ስኬቷ እንዲቀጥል ለኦሪገኑ ዓለም ቻምፒዮና ኢትዮጵያን እንደሚወክሉ ይፋ


በኦሪገኑ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ በተለያዩ ርቀቶች ጠንካራ ቡድን ይዛ ትቀርባለች፣

በተደረጉ በተለይም የወንዶች 10 እና 5ሺ ሜትር ተሳታፊዎች አትሌቶችን ጉዳይም አሰልጣኞች በጥንቃቄ ተመልክተውት ማሻሻያዎችን እንዳደረጉ ይታመናል።

በርቀቶቹ እየዳበረ የመጣውን የሌሎች አገራት አስፈሪ ተፎካካሪነት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለመግታት አቅሙም ብቃቱም አላቸው። ነገር ግን ይህን አቅም በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በነዚህ ርቀቶች እንደሚሳተፉ ይፋ ያደረጋቸው አትሌቶች አስደናቂ ብቃት ያላቸው ቢሆንም ማን በትክክለኛው ርቀት እንዲሮጥ ታስቧል የሚለው ላይ በርካታ ምክኒያታዊ ሙግቶች ይነሳሉ። የትኛው አትሌት በየትኛው ርቀት መሮጥ አለበት የሚለውን የሚወስነው አሰልጣኙ ነው። ለአሰልጣኞች ሙያዊ ነፃነት መስጠት እንደሚገባም አያከራክርም። ነገር ግን እንዳለፈው ቶኪዮ ኦሊምፒክ አሰልጣኞች አገርን ዋጋ በሚያስከፍል ደረቅ ሕግና ደንብ ታጥረው ውጤት ሲበላሽ በዝምታ ማለፍ ተገቢ ሊሆን አይችልም። አሰልጣኞች ይህን ስጋት ተመልክተው ተገቢውን ማሻሻያ ሲያደርጉም ማመስገን ባህል ሊሆን ይገባል።

በ5ሺ ሜትር ከተመረጡ አትሌቶች መካከል ወጣቱ በሪሁ አረጋዊ አንዱ ነው። ይህ ድንቅ አትሌት እኤአ በ2018 የታዳጊዎች የዓለም ቻምፒዮና ገና በለጋ ዕድሜው ፈጣን ሰዓት አስመዝግቦ ለአገሩ ሜዳሊያ ካጠለቀበት ጊዜ ጀምሮ በ10ሺ ሜትር ምን ያህል ልዩ ተሰጥኦ እንዳለው አስመስክሯል። በቶኪዮው ኦሊምፒክም በርካታ ጠንካራ አትሌቶች በተሳተፉበት ውድድር በሚደንቅ ብቃትና የቡድን ሥራ ብቸኛ ወርቅ እንዲመዘገብ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ዘንድሮ ግን በመጀመሪያው ዝርዝር ውስጥ በ5ሺ ሜትር ከሁሉም ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የተሻለ ፈጣን ሰዓት በማስመዝገቡ በኦሪገኑ ቻምፒዮና በዚሁ ርቀት ብቻ እንዲወዳደር ተመርጦ ነበር። ይህ አትሌት በመጀመሪያው ዝርዝር ውስጥ በ10ሺ ሜትር እንዲወዳደሩ ከተመረጡ አትሌቶች መካከል አንዱ አለመሆኑ ምርጫው ላይ ስጋት አሳድሮ ነበር። በመጨረሻው ምርጫ ግን ይህ አትሌት በ5 እና 10ሺ ሜትር እንደ ኢትዮጵያ ከ1 እስከ 3 ፈጣን ሰዓት ስላለው በሁለቱም እንዲሳተፍ መደረጉ አሰልጣኞች ከስህተታቸው የተማሩበት አንዱ ማሳያ ነው። የዓለም ቻምፒዮና የ5ሺ ሜትር ውድድሮች ታክቲክ የበዛባቸውና የማጣሪያ ፍልሚያም ያላቸው እንደመሆኑ አንድ አትሌት ለውጤት ለመብቃት የተሻለ ልምድ ሊኖረው እንደሚገባ ይታመናል። አንድ አትሌት ፈጣን ሰዓት መሮጡ ብቻ መታሰብ የለበትም። በዚህ ስሌት መሠረት በቶኪዮ ኦሊምፒክ ውጤት መበላሸቱ መዘንጋት የለበትም። በወቅቱ አትሌት ጌትነት ዋለ በ5ሺ ሜትር የኢትዮጵያ ፈጣን ሰዓት ስለነበረው ለኦሊምፒክ ተመርጦ ማጣሪያውን እንኳን ማለፍ አለመቻሉ በራሱ በቂ ትምህርት ነው። ይህ የተፈጠረው በርቀቱ የተሻለ ልምድና ብቃት ያለው ሰለሞን ባረጋ 10ሺ ሜትርን አሸንፎ በሙሉ የራስ መተማመን በቂ እረፍት ወስዶ በጥሩ ብቃት ላይ እንደሚገኝ እሱን ትቶ በወቅቱ ልምዱም ብቃቱም ያልነበረውን ጌትነትን ማወዳደር ስለተፈለገ ነበር። ይህ ዘንድሮ አለመደገሙ አሰልጣኞችን የሚያስመሰግን ሲሆን ኢትዮጵያም በርቀቱ አስፈሪ ስብስብ እንዲኖራት አድርጓል።

የኦሊምፒክ ባለድሉ ሰለሞን ቶኪዮ ላይ በዚያ የተሳሳተ ስሌትና ውሳኔ ክፉኛ ተበድሏል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ተቀይሟል፣ ተቆጥቷልም። በቶኪዮ 5ሺ ሰለሞን የቀነኒሳን ታሪክ የመድገም አቅም ነበረው፣ ግን የተሳሳተው ስሌት ታሪክ እንዳይሠራ ኢትዮጵያም በአንድ ወርቅ እንድትመለስ አድርጓል። አሁን ግን አሰልጣኞች ሰለሞንን የመካስ ዕድሉን በአግባቡ ተጠቅመዋል። በ5 እና 10ሺ ሜትሮች እንዲወዳደሩ ከተመረጡ አትሌቶች የመጨረሻ ዝርዝር ውስጥ መካተት ችሏል። ሰለሞን ዘንድሮ በሁለቱም ርቀቶች አስደናቂ ብቃት ላይ እንደሚገኝ ማሳየቱ በዓለም ቻምፒዮናው የኦሊምፒክ ቁጭቱን እንዲወጣና ኢትዮጵያም በርቀቶቹ የወርቅ ተስፋዋ ከፍ እንዲል አድርጓል። በተለይም በቅርቡ በተካሄደው የፓሪስ ዳይመንድሊግ በ5ሺ ሜትር የአየር ሁኔታው በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሳ የዓለም የርቀቱ የሁለት ጊዜ ቻምፒዮን ሙክታር ኢድሪስ እንኳን በውድድሩ መሃል ውሃ ለመጠጣት በተገደደበትና አንዳንዶችም መቋቋም አቅቷቸው ባቋረጡት ከባድ ፍልሚያ ላይ፣ ሰለሞን ብቻውን ከ13 ደቂቃ በታች 12፡56 ሮጦ ማሸነፉ ትልቅ ተስፋ እንዲጣልበት ያደረገ ነበር።

ከትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሚታተም

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT AND LOGISTICS

## ብዙኃኑን ታሳቢ ያደረገው «የታለመ የነዳጅ ድጎማ»

ቤዛ እሸቱ

በአገራችን ከዚህ ቀደም ተግባራዊ በነበረው ጥቅል የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ሳይለዩ ሁሉም የነዳጅ ምርት ተጠቃሚዎች በእኩል ተጠቃሚ የሆኑበት አግባብ ነበር። በዚህም የነዳጅ ዋጋ ከሚገባው በላይ ዝቅተኛ እንዲሆን መደረጉን ተከትሎ ለተለያዩ ብክነቶች ከማጋለጡ በተጨማሪ በመንግሥት በጀት ላይ ከፍተኛ ጫናን ፈጥሮ ቆይቷል።

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሯ ወይዘሮ ዳግማዊት ሞገስ እንደ አገር ነዳጅን በተመለከተ ምን ዓይነት አቅጣጫ ልንከተል ይገባል የሚለውን ለመወሰን ዝርዝር ጥናት መደረጉን ይገልጻሉ። በዚህም በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል ሙሉ በሙሉ ከድጎማ በአጠረ ጊዜ ማውጣቱ የራሱ የሆነ ጫና ይኖረዋል የሚል እምነት መያዙንና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት ለተወሰነ ጊዜ እንዲቀጥል ተወስኗል።

ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ተግባራዊ መሆን በጀመረው የታለመ የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ ለመሆን 164 ሺ 345 ተሽከርካሪዎች መመዝገባቸውን በትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የታለመ የነዳጅ ድጎማ አስተባባሪ የሆኑት አቶ አብዱልበር ሽምሱ ይገልጻሉ። ከዚህ ውስጥ ባለሦስት እግር (ባጃጅ) ቀዳሚ ሲሆን 115 ሺ 699 ተመዝግበዋል። ታክሲ 11 ሺ 320፣ አነስተኛ አገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች 17 ሺ 320፣ መለስተኛ አገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች 17


ፎቶ - ሀዲስ አብርሃ
አቶ አብዱልበር ሽምሱ

ሺ 118 እና 2ሺ 890 ባሶች ተመዝግበዋል።

የድጎማ አፈጻጸሙን ለመተግበር አምስት መስፈርቶች ታሳቢ ተደርገዋል። እነርሱም ተሽከርካሪዎች በቀን የሚጓዙት ኪሎ ሜትር፣ የነዳጅ ዓይነት፣ የተሽከርካሪ ዕድሜና የመያዝ አቅም፣ የመንገድ ሁኔታ የነዳጅ ፍጆታ ናቸው። አቶ አብዱልበር መስፈርቶቹን ሲያብራሩ አንድ ተሽከርካሪ በቀን ውስጥ ምን ያህል ኪሎሜትር ይጓዛል የሚለውን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተመደበው የነዳጅ መጠን ዕለታዊ እንቅስቃሴን የሚሸፍን እንዲሆን መደረጉን ይናገራሉ።

አቶ አብዱልበር የተሽከርካሪዎች ዕድሜና የመያዝ አቅም የታየበትን ምክንያትም ሲያስረዱ የነዳጅ ፍጆታ በተሽከርካሪ ዕድሜና በሚጭኑት ጭነት ልክ ስለሚለያይ መሆኑን ጠቅሰዋል። ተሽከርካሪው የሚወስደው የነዳጅ ዓይነትና የነዳጅ ፍጆታም የታየ ሲሆን ለዚህም የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ዓይነት ተለይቷል። ሌላው የመንገድ ሁኔታ ሲሆን ሁሉም ተሽከርካሪዎች በአስፋልት ላይ የሚሠሩ ካለመሆናቸው ጋር ተያይዞ ተሽከርካሪዎች የሚጓዙበት የመንገድ ሁኔታም ከግምት ውስጥ በመግባት ድጎማው መሠራቱን ይገልጻሉ።

እንደ አቶ አብዱልበር ገለጻ በመላው አገሪቱ በሥራ ላይ ከሚገኙ አንድ ሺ 17 የነዳጅ ማደያዎች ውስጥ ከ860 በላይ የሚሆኑት ማደያዎች የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተው አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ። በዚህም በአጠቃላይ በሀገሪቱ ከሚገኙት 85 በመቶ በላይ የነዳጅ ማደያዎች አገልግሎቱን የጀመሩ ሲሆን የተቀሩትም ከ15 በመቶ የሚያንሱ ማደያዎች አገልግሎቱን እንዲጀምሩ ይደረጋል። አንድ የነዳጅ ጣቢያ ወደ ሥርዓቱ አልገባም ማለት በአካባቢው የሚገኝ ተደጓሚ አገልግሎቱን አያገኝም ማለት ስለሆነ በልዩ ትኩረት የሚሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የታለመለትን የነዳጅ ድጎማ ሥርዓት ለማስተግበር እና በተቀናጀ የቁጥጥር ሥርዓት ለማስተዳደር የቴክኖሎጂ መተግበሪያ ኢትዮ ቴሌኮም በራስ አቅም በአጭር ጊዜ ውስጥ አበልጽጎ አቅርቧል። መተግበሪያው ለቁጥጥር በሚያመች እንዲሁም ብክነትን በሚያስቀር አግባብና የተጠቃሚዎችን ማንነት በቀላሉ መለየት የሚያስችል በመሆኑ ለነዳጅ አቅራቢውም ሆነ ለተጠቃሚው ቀላል እና ምቹ ነው።

### ለታለመለት የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሠጪ ተሽከርካሪዎች የተወሰነ ዕለታዊ የነዳጅ ፍጆታ

- ባለ ሦስት እግር (ባጃጅ) ተሽከርካሪዎች 7 ሊትር
- ኮድ 1 እና ኮድ 3 የከተማ ሚኒባስ ታክሲዎች 25 ሊትር
- ለአነስተኛ አገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች 65 ሊትር
- መለስተኛ አገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች 94 ሊትር
- ለከተማ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ 102 ሊትር
- ለፐብሊክ አውቶቡስ 25 ሊትር
- ለሀገር አቋራጭ አውቶቡስ 65 ሊትር

**9719**

**የታለመ የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ የሆኑ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ 9719 ላይ በነፃ በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ።**

የሚኒስቴሩ የማሕበራዊ ሚዲያ አድራሻዎች
ዌብሳይት፡- http://www.motr.gov.et/
ፌስቡክ፡- Ministry of Transport and Logistics - Ethiopia
ኢሜል፡- transportethiopia@gmail.com
ቴሌግራም፡- ministry of transport and logistics

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ